1377

# የተናቁ ዕንቁዎች

# CASTAWAY PEARLS



1377

437/2000

ቅርሳችንን ለማደስ

በመዲና ገ/ማርያም

# CASTAWAY PEARLS

# የተናቁ ዕንቁዎች

## CASTAWAY PEARLS

እውነተኛ ታሪክ

በመዲና ገ/ማርያም

ትርጉም ዐብይ ደምሴ
አርትኦት ምናሴ ጌታቸው

1990 ዓ.ም.

CASTAWAY PEARLS:–Claiming our Inheritance
Copyright 1995 by Medina Gebramariam

Second printing 1996

Printed In the United States of America.

የተናቁ ዕንቁዎች (ውርሳችንን ለማደስ)
የመጀመሪያ ዕትም እ.ኤ.አ 1995 ዓ.ም.
ሁለተኛ ዕትም እ.ኤ.አ 1996 ዓ.ም. **U.S.A** ታተመ

በ1990 ዓ.ም.
ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ
በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።

177

"አባቴና እናቴ ቢተውኝ እንኳን
እግዚአብሔር ዘወትር ይጠነቀቅልኛል ።"

መዝሙር 27:10



*Artwork by James R. Slade*

# ለመነሻ

እነሆ በዓለማችን አዲስ የታሪክ ጐህ በሚቀድበት ክፍለ ዘመን ላይ እንገኛለን። ታዲያ እኛም በተናቀውና በደካማው አቅማችን ከአንቀላፋንበት ተቀስቅሰንና ከአሸለብንበት ነቅተን አንድ ውል ያለው ነገር ለማበርከት መሸቀዳደም ይኖርብናል። ቢያንስ ቢያንስ ለነባር ወዳጆቻችን አለዚያም በአፍላ ለተዋወቅናቸው ግለሰቦች ወይም ሌላው ቀርቶ ለሚጠሉን እንኳን ቢሆን ልዩ ፍቅርና አክብሮት እንዳለን ማሳወቁ ፍቅራችንን ለምንገልጽለት ለዚያ ሰው ምንኛ ታላቅ መንፈሣዊ ድጋፍና ተሐድሶ እየለገስነው መሆኑን ምን ጊዜም ልንዘነጋው አይገባም።

እኔም ምንም እንኳን ዳጐስ ያለ ነገር ለመስራት ልቤ የተነሳሳ ቢሆንም ለጊዜው ይህችን በራሴ ሕይወት ዙሪያ የምትሽከረከር አጭር ጽሁፍ አቅርቤያለሁ። *(Cast Away Pearls)*

በማንኛውም ፀሐፊ የተዘገቡ ቃላት እስከተነበቡ ድረስ አንድም ድጋፍ አለዚያም ተቃውሞ ማጫርና ማስከተላቸው አይቀሬ ነው። እናም ይህች የእኔ ቁንጽል መጽሐፍ እንደአቅሟ የተለያዩ አስተያየቶችን መጋበዟም እሙን ነው።

የአንድን ጽሁፍ ጠንካራ ወይም ደካማ፣ ጤናማ አለዚያም ጉጂ ጉኖች አስመልክቶ መተቸች ተገቢ እንደመሆኑ ሁሉ በተለይም ስህተቶችን ሳይሸፋፍኑ መጠቆም ከማንኛውም አንባቢ የሚጠበቅ ነው እላለሁ።

*መዲና*

## የደራሲዋ መልዕክት

ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ሲሆን ስሜም መዲና ገብረማርያም ይባላል። የተወለድኩት ትግራይ ውስጥ በምትገኝ በሜጋሪያ ስበር መንደር ነው። ሜጋርያ ስበር የተቆረቆረችው በኤርትራና በኢትዮጵያ አዋሳኝ ሲሆን ከቀይ ባህር ያላት ርቀትም እምብዛም ነው።

በአካባቢዩ ባህልና ልማድ መሠረት አንዲት ነፍሰጡር ሴት በተገላገለች በሶስተኛው ቀን የወላዷ ልብሶችና ጨርቃ ጨርቆች በሙሉ ወደ ወንዝ ተወስደው ሲታጠቡ፣ እንግዳው አራስም ለመጀመሪያ ጊዜ የፀሐይ ብርሐን እንዲያይ ይደረጋል። ይህም የራሱ የሆነ በዓልና ሥርዓት አለው። ሕፃኑ በተወለደ በሰባተኛው ቀን (ወንድም ቢሆን ሴት) በምላጭ ካልተገኘም በባልጩት ወይም በሱፋጭ ይገረዛል። ይህም የሚፈፀመው በባለሙያ ሐኪም ሳይሆን በመንደር ወጌሻ አማካኝነት ነው።

ሕፃኑ ወንድ ከሆነ በተገረዘ በሰላሳኛው ቀን ወደ ቤተክርስቲያን ተወስዶ ሥርዓተ ጥምቀት ይፈፀምለታል። ሴት ከሆነች ግን ክርስትና የምትነሣው በተወለደች በሰማንያ ቀን ይሆናል።

የገጠሩን የሀገራችንን ክፍል እንደ መርግ የተጫነውና አሁንም ድረስ የሚሰራበት ያልተናደው ጐጂና አስከፊ ባሕል

በሴቷ ላይ ባለው ጫና መሰረት ገና ሶስት ዓመት እንደሞላት በቤተሰቧ ስምምነት ለባል ትታጫለች። ለመታጨቷ ምልክት እንዲሆናትም በአንገቷ ላይ የብር ሀብል ይንጠለጠልላታል።

ሕጋዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት የሚፈፀመው ግን ዕድሜዋ ሰባት ዓመት ሲሞላት ሲሆን ከዚያ በኋላ ለተጨማሪ ሶስት ዓመታት እየተጠበቀች እንድትኖር ይደረጋል። ሆኖም በይፋ የትዳር ሕይወቷን የምትጀምረው በአሥር ዓመት እድሜዋ ሲሆን በዓመቱም የልጅ እናት ትሆናለች። ገና በአስራ አንድ ዓመቷ ሰውነቷ ሳይጠነክርና አዕምሮዋም ሳይበስል ምንም ዓይነት ዘመናዊ የሕክምና አገልግሎት በሌለበት ስፍራ አን ድም በወሊድ ትሞታለች አለዚያም ያለ ዕድሜዋ በተፈጠረ እርግዝናና ምጥ ሳቢያ የእድሜ ልክ በሽተኛ የመሆኗ አጋጣሚ የሰፋ ይሆናል።

በሌላም በኩል እንደ ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ዕምነትና ባህል ለማንኛውም ሕመም ፈውስ የሚገኘው እግዚአብሔርን በመማፀን ነው። ያም ቢሆን አልፎ አልፎ መድሐኒትነት እን ዳላቸው በሚነገርላቸው ዕጾችና ሥራሥሮች መጠቀማቸው አይቀርም። ለምሳሌ እኔ በተወለድኩበት አካባቢ ለራስ ምታት ሕመም ማስታገሻ ሲባል ከግንባር ላይ ሥር በጥቶ ደም እንዲ ፈስ ማድረግ እስከ አሁን ድረስ በመፍትሄነቱ ይታመንበታል።

ውጋትና ቁርጠት ለመሳሰለውም ደዌ በጣጣቴ መተከስና በዋግምት መነጠቅ በእጅጉ የተለመደ ሲሆን የአጥንት ስብራት በሚያጋጥማቸውም ጊዜ የባሕል ወጌሻው ጠግኖ ያስረዋል። ከዚህ ሁሉ ሙከራ በኋላ በሽተኛው ከሕመሙ ያላገገመ ከሆነ የመጨረሻ ተስፋና መጽናኛቸው ጠበል ወደሚገኝበት አንዱ ገዳም በመሄድ መጠመቅና መጠጣት ይሆናል።

ይህን መሰሉ ልምድ አሁንም ድረስ እንደቀጠለ ነው። አሁንም የእኔን የትውልድ መንደር በምሳሌነት ብወስድ ሐኪም ወይም ቀይመስቀል ጭራሹን ጉብኝቷት አያውቅም። እንዲህ ዓይነቱን እርዳታ ለማግኘት ከተፈለገ የቀናት መንገድ በከብት ጀርባ አለዚያም በእግር መጓዝ ግድ ነው። በዚህ ሳቢ ያም ሕመምተኛው ምንም አይነት የሕክምና እርዳታ ሳያገኝ እቤቱ እያለ አለዚያም በጉዞ ላይ ሕይወቱ የሚያልፍበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም።

እንግዲህ የሶስተኛው ዓለም ሕይወት ከሞላ ጎደል ይሄን ሲመስል በአንፃሩ የሠለጠነውና ነፃው ዓለም ግን ከከፍተኛ የእ ድገት ደረጃ ላይ በመድረሱ ለእነዚህ ጉስቋላ ሕዝቦች ተገቢ ውን እርዳታ ሊያደርግ ይገባል። ቢያንስ ቢያንስ በአርአያ እግ ዚአብሔር የተፈጠሩ አምሳያ ወገኖቹ መሆናቸውን ማስታወስ አለበት።

እኔም የእግዚአብሔር ፈቃድ እስከሆነ ወደ ትውልድ አገሬና መንደሬ በመመለስ በተለይ አሳዳጊ ላጡት ዕጓለማውታን በማቋቋም ተገቢውን እንክብካቤ የማድረግ ዕቅድ አለኝ። በእግዚአብሔር ፈቃድ አሁን ካለሁበት ደረጃ ለመድረስ ብችልም በአንድ ወቅት እኔም እንደእነሱ ምስኪን ነበርኩኝና ችግራቸው ሁሉ ይሰማኛል።

ከዚህ የሚቀጥለው ታሪኬን ለማንበብ ፈቃደኛ ስለሆናችሁ ሁሉ ታላቅ ምስጋና አቀርባለሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

በፍቅር እወዳችኋለሁ:-

መዲና

## መግቢያ

ውብና ለምለም ሀገራችን የአፍሪካ ቀንድ የሚባለውን የአህጉሩን ክፍል በስፋት ከመሸፈንዋም አልፎ የታላቁ የዓባይ ወንዝ መፍለቂያ ምንጭ ናት። ያም ብቻ አይደለም በአያሌ ወንዞችና ጅረቶች የተሸነሸኑ ጥልቅ ሸለቆዎች የሚያቆራርጧት፣ የናይልን ወንዝ ለማንያ በመቶ የሚመግቡ ፈሣሽ ጅረቶች የሚንዶለዶሉባትም ጭምር ናት።

የጐብኝዎችን ልብ ጠልፈው የሚያማልሉ ብርቅዬ የዱር አራዊቶቿ በተለይም በሌላው የዓለም ክፍል የማይገኙ እንደ ሰሜን ቀበሮና ዋሊያ የመሳሰሉት በሰሜኑ ተራራ ላይ ይርመሰመሱበታል። ከየትኛውም አካባቢ ለየት ያሉ ጃርቶችና የዝንጀሮ መንጋም ያለ አንዳች ሥጋት ጐን ለጐን ሲሰማሩ ማየት ምንኛ ደስ ይላል። ይህም ሌላው ድንቅ የተፈጥሮ ችሮታ ነው።

በሌላም በኩል ይህች በተፈጥሮ ሀብቷ የታደለች ሀገር የብሔሮች፣ የቋንቋዎችና የባሕሎችም ማዕከል ናት ለማለት ይቻላል። በአሁኑ ሰዓት በአገሪቱ ውስጥ ከዘጠና በላይ ቋንቋዎች እንዳሉም ይገመታል።

በመሆኑም በአሜሪካ የሚገኙ የአፍሪካዊያን ሁለተኛና ሶስተኛ ትውልዶች እንደሚገምቱት ሳይሆን ኢትዮጵያዊያን

እርስ በርሳቸው ተፋቅረው የሚኖሩ ብልህና አስተዋይ ሕዝቦች ናቸው። ለዚህም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከራሱ ብሔር ቋንቋ ውጭ ሁለትና ሶስት ከዚያም የበለጠ የሌሎች ብሔሮችን ቋንቋ መናገርና መረዳት መቻሉ አንዱና አቢይ ማስረጃችን ነው።

በሃይማኖታችንም ረገድ ቢሆን ይሄ ነው የሚባል ልዩነት ስንፀባረቅ አናይም። ምንም እንኳን ከፍተኛ ቁጥር አለው ተብሎ የሚገመተው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ክፍል ቢሆንም አያሌ የእስልምና እምነት ተከታዮችም ሆኑ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች በመግባባትና በመቻቻል የሚኖሩባትም ሀገር ነች። የየትኛውም ዕምነት ተከታይ ቢሆን ለእምነት ክብርና ከፍተኛ ፍቅር አለው ስለዚህም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ለፈጣሪው ፀሎት ለማድረስ ሲል በየሳምንቱ ሁለቴና ሶስት ጊዜ ሰማይ ጠቀሱን የሰሚን ተራራ ውርጭና ቆንጥሩ ሳይበግረው ገደሉን እየቧጠጠ የሚወጣውን ሕዝብ ማየቱ በእጅጉ የሚያስገርም ነው።

ሀገራችን በ1950ዎቹ ዓ.ም. መጀመሪያ በሁሉም መስክ ኋላ ቀር ሀገር ነበረች። የትምህርትና የሕክምና አገልግሎት በተለይ በባላገሩ ሕዝብ ዘንድ ፈጽሞ ያልተለመደ ነበር። ምንም እንኳን በ1960 ዓ.ም አካባቢ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ መጠነኛ የሆነ መሻሻል ቢታይም የንጉስ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ወድቆ አገሪቱ በኮሚኒስቶች ቁጥጥር ሥር በመዋሏ ሊበራ ጭል ጭል ይል የነበረው የሥልጣኔ ብርሃን እንደገና ደበዘዘ። ከፍተኛ ተቋማት፣ ባንኮች፣ ኢንዱስትሪዎችና ሰፋፊ እርሻዎች፣ የከተማ ቤትና ቦታ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በመዋሉ ጤናማ የነበረው የአገሪቱ የእድገት አቅጣጫ ተገታ። በዚህም ሳቢያ ከ500,000 የሚበልጡ ቤተሰቦች በመንግስት እርሻዎች ላይ ያለውድ በግድ እንዲሰማሩ ተደረገ።

ይህን መሰሉ አሉታዊ እርምጃ ዓለም አቀፋዊ ውግዘትን ማስከተሉ ባይቀርም አምባገነኑ መንግስት ግን በቀላሉ የሚንበረከክ አልነበረም። ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የነበረውን የግብርናውን መስክ (በተለይ ቡናን) በመቆጣጠርና የሕዝቡን ፖለቲካዊ ሕይወት በአመራሩ ስር ለማዋልም ሞከረል። ሆኖም ይህ ሁሉ ሁኔታ ሕዝባዊ ተቃውሞን በማስከተሉ የእርሻው ምርት በእጅጉ አሽቆለቆለ። በሌላም በኩል አገሪቱ ላልታሰበና በአጭር ሊቀጭ ላልቻለ የእርስ በርስ ጦርነት ተዳረገች። እንደ ሰደድ እሳት የተዛመተው ረሀብም ለሁለት ሚሊዮን ዜጎች ሕይወት መቀጠፍ ምክንያት ሆነ።

ምንም እንኳን የችግሩን አስከፊነት የተረዱ እርዳታ ለጋሽ ሀገሮች በሚሊዮን ቶን የሚገመት የእርዳታ እህል ወደ አገራችን ቢያጎርፉም የረሀቡን ወረርሺኝና ወደ ጎረቤት ሀገር ሱዳን የተደረገውን የ700,000 ሕዝብ ስደት ለመግታት አልተቻለም።

በመጨረሻም በእግዚአብሔር እርዳታ ያመንግስት ተወግዶ በምትኩ ለእኩልነትና ለሰብዓዊ መብት መከበር ትኩረት ተሰጥቷል ።

## ክፍል 1

### ምዕራፍ :- 1

### የልጅነት ዘመኔ

ታሪኬን ከግርዘቴ የጀመርኩት ከመሠረቱ ልነሣ ብዬ እንጂ ሌላ ምንም የተለየ ጉዳይ ኖሮኝ አይደለም። እንደ ጥንቱ የሀገራችን ባሕል ሁሉ እኔም በአንዲት በዕድሜ የገፉ የመን ደራችን ሴት ገና የሰባት ቀን አራስ እያለሁ ነው የተገረዝኩት።

ወላጆቼም አጥባቂ ክርስቲያን እንደመሆናቸው መጠን ክርስትና የተነሳሁትም እንደማናቸውም ሁሉ በተወለድኩ በሰማንያ ቀኔ ነው።

ስድስት ዓመት እስኪሞላኝ ድረስ እናቴ እየተንከባከበች እንዳሳደገችኝ ይታወሰኛል። ሆኖም ግን ይቺ የምትወደኝ እናቴ በዚሁ እድሜ ላይ እንዳለሁ ሳይታሰብ በድንገት በመ ሞቷ ከዚያን ወዲህ ያለው የእኔም ሕይወት ጨለማ ተጋረ ደበት። እንደ እውነቱ ከሆነ እኔም ከእሷ ጋር አብሬ ሞቻለሁ ማለቱ ይቀለኛል። በአካል ሕያው ብሆንም መንፈሴ ግን እጅግ የተጐሳቆለና የተራቆተም ነበር።

ያንን ያህል የስቃይ ዘመንና ሕይወት በትዕግስት ለማሳለፍ ያስቻለኝ ያለ ጥርጥር በእግዚአብሔር መተማመኔ ብቻ ነው።

አሁን ላለሁበት ሕይወትና ለምገኝበትም የአሜሪካን ምድር ያበቃኝም የእግዚአብሔር ፀጋና በረከት መሆኑን አምናለሁ። ለእናንተም ይሄ የፈጣሪ ፀጋና በረከት እንዲበዛላችሁ የምን ጊዜም ፀሎቴ ነው።

ባዘንን፣ በተከዝን፣ ተስፋ በቆረጥንና ሁሉም ነገር የጨለመ በሚመስለን ጊዜና ሰዓት ብርሐናችንና መጽናኛችን እግዚአብሔር ብቻ ነው። እርሱ የተዘጋውን በር በመክፈት ወደ መልካም ጉዳና ይመራናል።

እኔም በዕድሜዬ ከፍ ስል እንደተነገረኝ ገና ከሕይወት ጅማሬ ከአስከፊ አደጋ አምልጫለሁ። እናቴ አጥባቂ የቤተክርስቲያን ሳሚ ናት። አንድ ማለዳ እናቴ ሁሌም ወደምትሳለመው ቤተክርስቲያን በሄደችበት ጊዜ የቤት አገልጋያችን እኔን በአንቀልባ አዝላ እንጀራ ለመጋገር ደፋ ቀና ስትል ሳይታሰብ ከጀርባዋ ላይ ተንሸራትቼ እሳት ላይ ወድቄ ኖሮዋል፤ በዚያ እሳት ከተለበለበው ቁስል ለመዳን አንድ ዓመት ከመንፈቅ ከመፍጀቱም በላይ የቁስሉ ጠባሳ ዛሬም ቢሆን ማስታወሻዬ ሆኖ በጀርባዬና በእናቴ ላይ እንደተሸከምኩት እኖራለሁ።

ምንም እንኳን ለቤተሰቤ አራተኛ ልጅ ብሆንም በዚያ የጨቅላ ዕድሜዬ ከአዋቂዎች ጋር መዋልና እንደነሱም መናገር



የሚሰጠኝ ደስታ ልዩ ነበር። ስላለፈው የሰዎች ታሪክ የማወቅ ፍላጎቴም ወደር አልነበረውም። ይህን ሁኔታዬንና ቅብጥብጥ ባህሪዬን በቅርቡ የምታውቀው እናቴ ከወለደቻቸው ዘጠኝ ልጆቿ እኔ የተለየሁ ስለመሆኔ ደጋግማ የምትነግረኝ ሁሉ ትዝ ይለኛል። ያለፍኩበትን የሕይወት አቀበትና ቁልቁለት ሳስበው ና አሁን ያለሁበትን ደረጃ ከሕሊናዬ ሚዛን ላይ ሳሰፍረው እናቴ እውነትም ትክክል ነበረች።

አንድ ቀን ወላጆቼ እኔንና ሌሎች ሶስት ልጆቻቸውን ዘመድ ለመጠየቅ ራቅ ወዳለ መንደር ይዘውን ሄዱ። ምንም እንኳን የጉዞዋችን እቅድ ሁላችንም በእንግድነት የሄድንበት ቤት ውለን ለማደር ቢሆንም እናቴ ግን ለቤቷና ለቀሪ ልጆቿ በማሰብ ከእኛ ጋር በማደር ፋንታ ያንኑ ቀን ወደ ቤት ብቻዋን ተመለሰች። ያቺ ዕለትና ያቺ አጋጣሚ ነች ለጋ የጋሜነት ዕድሜዬ በችግርና በስቃይ እንዲፈተን በርከፋች የሆነችው። እንደተነገረኝ ከሆነ እናቴ ወደ ቤት ተመልሳ ሌሊቱን በጠና ታማ አደረች። ሊነጋጋ ሰማይ ሲያቅላላ አረፈች።ያቺን የምወዳትና አሳቢ እናቴን ዳግመኛ ላላያት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተለያየን።

አባቴም በዛች ትንሽ መንደር ሀብት አላቸው ከሚባሉት አንዱ ስለሆነ ቤታችንም የሞቀ፣ ግቢያችንም በጋማና በቀንድ

ከብቶች የሞላ ነበር። ያም ሆኖ ግን በእናቴ ሞት ምክንያት የእ ኔን፣ ገና የስድስት ዓመት ልጅ የሆንኩትን የመዲናን የቆሰለ ልብ ሊያሽር ቀርቶ ሊያጽናና የሚችል ምንም ነገር አልነበ ረም። ይብሱኑ ሕይወቴ የበለጠ የሀዘን ድባብ አደባበት።

ቀናትን የማሳልፈው እንዳለቀስኩና እንደተከዝኩ ነው። በተለይም ያ ገራገር ገጽታዋና ሁሌም አይተው የማይጠግቡኝ ዓይኖቿ በድንገት ከፊቴ ድቅን ሲሉ ድምፄን አውጥቼ እዬዬ እላለሁ። መንደርተኛውም ሁሉ ልቅሶዬን ሲሰማ አብሮኝ ማል ቀስ ይጀምራል። ምኞቴ ሁሉ እኔም ቶሎ ሞቼ ከእናቴ ጋር ለመገናኘት ስለነበር ምግብ አልበላም ነበረ። በዚህም የተነሳ በክሳት አጥንቴ እስከሚቆጠር ድረስ ደረቅሁ።

ያን መሰሉ የሞቀና የደመቀ ቤትም በሀዘን ጥላሸት ጠለሸ። ምናልባት ትዳር የያዙት ታላላቅ እህቶቼ ጊዜውን እንዴት እን ደሚያሳልፉት ባላውቅም እቤት ያለነው ግን እንደተኮራረፈ ሰው ማዶና ማዶ ሆነን ለየብቻችን ተኮራምተን ስንቆዝም ነበር የምናሳልፈው። ይሄን አስከፊና መራራ ሁኔታ ለስድስት ወራት ያህል ገፋሁት።

አንድ ዕለት ከዚያ በፊት አስቤው የማላውቀው ሀሳብ በድንገት ፍንትው አለልኝ። ይሄውም እናቴ አልፎ አልፎ ትዳር የያዙትን ታላላቅ እህቶቼን ለመጠየቅ ስትሄድ



አብሬያት እሄድ ስለነበር ወደ አንደኛዋ እህቴ ቤት ጠፍቼ ለመሄድ ወሰንኩ። ከቀናት በኋላም ማንም ሳያውቅብኝ ወደ እህቴ ቤት የሚወስደው መንገድ ተያያዝኩት። በጉዞዬም ላይ አንዳንድ መንገደኞች ከመታየታቸው በስተቀር ጉዳናው ጭር ያለ ነው፣ በመሀሉ በድንገት እየመጣ ከሚያስጨንቀኝ የፍርሀት ስሜት ለመገላገል እራሴን በእራሴ እያደፋፈርኩት ከግማሽ ቀን ጉዞ በኋላ ከእህቴ ቤት በሰላም ደረስኩ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ያቺ የልጅነት ልቤ ብዙ ብዙ ነገር አስባ ነበር። ማሰብም ብቻ አይደለም ተመኝታም ነበር። ቢሆ ንም ግን እህቴ ዘንድ ቀላልና የተመቻቸ ነገር አልገጠመኝም። ከምንም በላይ ደግሞ ለምንና እንዴትስ ወደ እርሷ እን ደመጣሁ እህቴን ማሳመኑ ምንኛ ከባድ ነበር።

ሆኖም በተቻለ መጠን የችግሬንሁኔታ ተረድታ አብሬያት እንድኖር እንድትፈቅድልኝ እያለቀስኩ ተማፀንኳት። በመ ጨረሻም የልጆቿ አሳዳጊ ሆኜ እንዳገለግላት የምስማማ ከሆንና ማናቸውንም የቤት ውስጥ ሥራ ለማከናወን ፈቃደኛ ከሆንኩ አብሬያት መኖር እንደማትከለክለኝ ገለፀችልኝ።

የቤት ውስጥ ሥራው ከባድ ነው። በተለይም ከዕድሜዬ ጋር አይመጣጠንም ከብቶች ማሰማራት፣ ከወንዝ ውሃ መቅ ዳት፣ እንጨት መስበሩና ምግብ ማብሰሉን የመሳሰሉት

ሥራዎች በሙሉ በእኔ ትከሻ ላይ የተጣሉ ኃላፊነቶች ሆኑ። ምንም እንኳን እራሴን ለባርነት ሕይወት አሳልፌ መስጠቴ ቢታወቀኝም ይህን መሰል መከራ ከእህቴ ይጠብቀኛል ብዬ ግን ለአፍታ እንኳን አስቤው አላውቅም።

እኔው እራሴ የስድስት ዓመት ሕፃን ሆኜ ሌሎቹን ሕፃናት መመገብና መንከባከብ ነበረብኝ። ከዚህ ሁሉ በላይ እህቴ ምክንያት እየፈለገች ጀርባዬ እስኪደማ ድረስ ትገርፈኛለች። የሚያሳዝነውና አሁንም ሳስበው መልስ የማላገኝለት ጥያቄ እህቴ ለምን እንደዚያ ታደርግ እንደነበረ ነው። ሁኔታው ሁሉ እየከበደኝና ከምችለው በላይም ስለሆነብኝ ምንም እንኳን መራራና አስከፊ ነገር እንደሚጠብቀኝ ባውቅም ወደ አባቴ ቤት ለመመለስ ወሰንኩ።



# ምዕራፍ:-2

## ልማድ ሲፋለስ

ከእህቴ ቤት ተሰቃየሁ ብዬ እንዳልወጣሁ ሁሉ ዳግመኛ ለባሰ ጭንቅና መከራ ተዳረግሁ። ወደ አባቴ ቤት መመለሴም በእንጀራ እናት ቁጥጥር ስር ለመዋል ሆነ።

በቆየው ባህልና ልማዳችን መሰረት በሕጋዊ ጋብቻ ተሳሰረው ልጆች ከወለዱ በኋላ ከባል ወይም ከሚስት አንደኛቸው በሞት ቢቀድሙ ዳግመኛ ሌላ የትዳር ጓደኛ መያዝ የተከለከለ ነበር። ሕፃናቱን መንከባከብና ለወግ ማብቃትም በሕይወት ላለው ሰው የተተወ ነው። ሆኖም ግን አባቴ የዚህን ተቃራኒ አቋም ለመያዝ መረጠ። ከሌላ ባል ሶስት ልጆች ወልዳ የነበረችን ሴት ለማግባት ወሰነ። ለዚህም የሰጠው ምክንያት እኛን ተንከባክባ እንድታሳድግለት ባለው ጽኑ ፍላጐት መሆኑን ገለፀልን።

ሆኖም የእንጀራ እናታችን አንዳችንንም አትወደንም ለአባታችን ግን ፍቅሯን ለግሳዋለች። በምታደርግለት እንክብካቤም ተሸንፏል። ስለዚህም ለእኛ የሚጣልልንን የከረመ ፍርፋሪ ለማየትና ለማዘን ዓይኖቹ ተዘጉ። በስራው ምክንያትም ከአካባቢው ርቆ ስለሚሄድም በእኛ ላይ የሚፈፀመውን በደል

ጆሮዎቹ ሊሰሙ ተሳናቸው። እኛም የሚወረወርልንን እንበላለን፡ የምንታዘዘውንም ያለአንዳች ማንገራገር እንሰራለን።

አይ! አንተ አምላክ ለምን እንደዚህ አደረክ? በማለት በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ወዳለበት ሰማይ ቀና አልኩኝ። ዘንበል እንዲልልኝም ጠየኩት። «ታገሺ አለኝ።» ግን እስከመቼ?

ይሄ ያለርህራሔ የሚፈፀምብን በደልና ግፍ ከአባቴ ቤት ለዳግመኛ መኮብለል ምክንያት ሆነኝ። የአሁኑ ስደቴ ጉዞው እጅግ አድካሚ ቢሆንም የእግዚአብሔር ሙሉ ጥበቃና እንክብካቤ የታከለበት ነበር። ሶስት ቀን የሚፈጀውን ተራራና ሸለቆ ሜካና በረሃ ማለፍም ግድ ነበር። ቢሆንም ሌሎች መንገደኞች አጋጥመውኝ ስለነበር ብቸኝነት ሳያጠቃኝ ውሃ ጥምና ርሃብ ሳይፈራረቅብኝና መጠለያ ሳላጣ በደህና ከሌላኛዋ ባለትዳር እህቴ ቤት ደረስኩ።

ይሄ ሁሉ በእግዚአብሔር ተዓምር የተፈፀመ እንጂ እንደ እኔ ብቸኝነት ቢሆን ከአንዱ ፈፋ ስር ወድቄ በቀረሁ ነበር። ያም ሆኖ ግን ሰውነቴ እጅግ በመጐሳቆሉና በመጠቋቆሩ የገዛ እህቴ እንኳን በቀላሉ ልታውቀኝ ተቸግራ እንደነበር አስታውሳለሁ።



# ምዕራፍ:-3

## ጭቅጭቅ

የአሁኑ ስደቴ ካለፉት ሁሉ የተለየና የተሳካም መሰለኝ። እህቴ ለጊዜውም ቢሆን ያደረገችልኝ አቀባበልና እንክብካቤ ለተጐሳቆለው ሰውነቴ በመጠኑም ቢሆን ተስፋ ሰጪ መሰለኝ። ይሁን እንጂ ቀናቶች ባዘገሙ ቁጥር ነገሮች ሁሉ መለዋወጥ ጀመሩ።

የእህቴ ባል ስለ እኔ ምንም መልካም ነገር እንደሌለው መረዳት ለኔ ቀላል ነበር። የሚያየኝ ሁሉ በጥላቻና በሚያመ ናጭቅ ገጽታው ነው። በባለቤቷ ድርጊት ቅር የተሰኘችው እህቴ ያላት ምርጫ አንድ ብቻ ሆነ። እሱም እኔን ወደ አባቴ ቤት እንድመለስ ማድረግ። እኔም ሌላ አማራጭ የለኝምና እን ደመቃብር ጉድጓድ ወደሚያስፈራኝ የአባቴ ቤት መመለስ ግድ ሆነብኝ።

ከተመለስኩ በኋላም ብዙ አልቆየሁም። አንድ ቀን አባቴ ሳላስበው በድንገት ለጉዞ እንድዘጋጅ ነገረኝ። ለጊዜው ወዴት እንደምሄድ ባላውቅም በውስጤ ግን ብዙ ነገሮችን ማሰላሰል ጀመርኩ። አባቴም ፊቱን የመለሰልኝ መሰለኝ። እናቴ በሕይ ወት በነበረች ጊዜ ሁለቱም በጋራ ለእኛ የነበራቸው ፍቅር

አባቴ ላይ የተቀሰቀሰ መሰለኝ። እናም በውስጤ ሃሴት አደረኩ።

ምንም እንኳን የምሄድበትን ቦታ ባላውቅም ጉዞዎችን ግን ቀላል አልነበረም። ከአካባቢያችን እጅግ ወደራቀ መንደር ደረስን ከአንድ ቤተሰብ ጋር ካገናኘኝ በኋላ አመሌን አሳምሬ ከእነሱ ጋር መኖር እንዳለብኝ ማስጠንቀቂያ አዘል ትዕዛዝ ሰጥቶኝ ትቶኝ ሄደ። ቀደም ሲል ስለዚህ ቤተሰብ አንዳችም ነገር ሰምቼ አላውቅም፤ የሥጋ ዝምድናም ስለሌለን በአጭሩ ለዚያ ቤተሰብ እንደ ባርያ የተሸጥኩ አለዚያም በሽልማት መልክ የተሰጠሁ ገፀ በረከት መሆኔ ነበር።

እንደምንም የሚደርስብኝን ስቃይና መከራ በመታገስ ለስድስት ወራት ያህል በዚያው ቆየሁኝ። በእነዚያ የቆይታዬ ወራቶች ውስጥ ከሁሉም ያስመረረኝ የሚደርስብኝ ዱላና የስራ ብዛት ሳይሆን «ይቺ እናቷን የገፉች፣ ለወላጅ አባቷ ያልሆነች እርጉም!» እያሉ የሚያመመናትሉኝ ነበር። ስለዚህም ምሳና ቁርሴ በእንባ የራሰ እንጀራ ሆነ።

የሞት ጥላ የእኔን ትከሻ ተንተርሶ እቤት ውስጥ የሚያድርም ይመስል በምሽት በር እየዘጉ ሲያባርሩኝ ብዙውን ሌሊት የማሳልፈው በየታዛውና በየጉተራው ሥር በመተኛት ነበር። በዚህ መሰሉ ሁኔታ በተላለ በዱር አውሬ ልበላ አለመቻሌ በአያሌው የሚገርም ነው።



ታዲያ! ይሄ ሁሉ ግፍ ያነሰ ይመስል አንድ ቀን ባልና ሚስቱ፣ (ገገርዎቹ ብል ይቀለኛል።) ክፉኛ ስለደበደቡኝ ሕይወቴ በሞት አጣብቂኝ ውስጥ ገባች። እራሴንም ሳትኩኝ። ለብዙ ቀናትም የአልጋ ቁራኛ ሆንኩ። አባቴም የደረሰብኝን ችግር ሰምቶ ስለነበር መጥቶ ይዞኝ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ሕይወቴም ሊውጣት ካሠፈሠፈ ሞት አፈተለከች።

በአባቴ ቤት ከጉዳቴ ለማገገም ቀላል አልሆነልኝም። ከሞት መዳኔ ግን በራሱ አስገራሚ ነበር። ቢሆንም ገና በማገገም ላይ እያለሁ ያ ክፉ ዕድል አለቀቀኝ ኖሮ አሁንም ዳግመኛ በአባቴ አስገዳጅነት ወደ አድዋ ከተማ ተወሰድኩኝ። በዚያም ለአንዲት ምግብና መጠጥ በመሸጥ ለምትተዳደር ሴትኛ አዳሪ አሻሻጭ እንድሆን አስረከቦኝ ተመለሰ።

ውድ አንባቢዎቼ: እዚህ ላይ አንድ ነገር ለማለት እፈልጋለሁ፤ ይኸውም አባቴ ለዚያች ሴትኛ አዳሪ አሻሻጭ እንድሆን አስረከቦኝ በምንሰነባበትበት ወቅት የሰጣት ማስጠንቀቂያ ነበር። ስለ እኔ ወላጆች ማንነት ለማንም እንዳትናገር ከዚያ በተረፈ ግን እንደ ግል ባርያዋ ልትጠቀምብኝ እንደምትችል ሙሉ ሥልጣን እንዳላት ገለፀላት። ከእኡም ጋር ቢሆን ለመጨረሻ ጊዜ መቆራረጡን በነገረኝ ወቅት ምርር ብዬ አለቀስኩ። ዛሬም በዙፋኑ ላይ ወደተቀመጠው አምላኬ ቀና

አልኩኝ። ዘንበል እንዲልልኝም ጠየኩት አሁንም [illegible] ታገሽ አለኝ። ግን እስከመቼ ?

ከሶስት ወራት ቆይታም በኋላ ወደ አሥመራ ለመሄድ አቅዳ ኖሮ ይዛኝ ልትሄድ ተነሳች። ይህን ስሰማ በመጠኑም ቢሆን የጨለመው ተስፋዬ ዳግም የብርሐን ጭላንጭል ፈነጠቀበት። ማን ያውቃል? በዚያ እጅግ ሰፊና ብዙ ሕዝብ በሚኖርበት ከተማ ውስጥ እግዚአብሔር ለእኔ ያመቻቸው ያተሻለ ዕድል ይኖርም ይሆናል ብዬ አሰብኩ። ስፍራ መቀየርም በሕይወቴ ላይ ለውጥ ሊያስከትል ይችላል የሚል የፀና ውስጣዊ እምነት አሳደረብኝ። አይ ልጅነት! አሥመራ እስክንደርስ ድረስ የቱን ያህል ቸኩዬ ነበር!



# ምዕራፍ :- 4

## የተስፋ ጭላንጭል:

ለጉዞዋችን አስፈላጊ የሆነው ሥንቅ ተሰንቋል፣ ልብሳችንና የቤት ቁሳቁሳችን ሁሉ በየመልኩ ታስሮ ተዘጋጅቷል፤ ምናልባትም የቀረን ነገር ቢኖር እኔን ይዛ ወደ አሥመራ መሄዷን ለአባቴ ማሳወቅ ብቻ ነው። ይሄም ቢሆን እንደ ፈለግሽ አድርጊያት ተብላ ለተሸጠች የሰባት ዓመት ልጅ ምንም አስፈላጊ አልነበረም።

የሚገርመው እሷም ለምን ይሄን እንዳሰበች እንኳ እንኳ ለአባቴ ለመንገር ፈቃደኛ አልነበረችም። እኔም የአባቴ ጉዳይ ለእሷ ሲሰጠኝ በነገራት ነገር ከሆዴ የወጣ ስለሆነ ጉዞዬን በተመለከተ መስማትና አለመስማቱ ያን ያህል የሚገደኝ አልነበረም።

እንደውም ጉዞዋችንን ባሰብኩ ቁጥር በልቤ የሚሰማኝ ደስታ ልዩ ሆነ። አንድ አሌ የማልለው ያደረብኝ ፍርሀት ግን አለ። እሱም ከዚያ በፊት በማንኛውም ዓይነት መኪና ተሳፍሬ ስለማላውቅ የሚጠብቀኝ የአውቶቡስ ጉዞ ምን ይመስል ይሆን? ስል አስባለሁ።

ያ በናፍቆት ስጠብቀው የነበረ የመሄጃችን ቀን ደረሰና
ሕፃን ልጇን አሳዝላኝ ወደ አውቶቡሱ መናኸሪያ አመራን።
አውቶቡሱ ላይ እንደተሳፈርንም ሕፃኑን ከጀርባዬ ላይ አው
ርዳ ከታቀፈች በኋላ እኔን በጉልበቶቿ መሀል ወሽቃ ከወለሉ
ላይ አስቀመጠችኝ። በዚህም አላበቃችም፣ ቀሚሷን ከፍ አድ
ርጋ እንዳልታይ ሸፈነችኝ። ሕፃኗን ከጉያዋ ተወሽቆ ባቀረቀረ
አንገቴ ላይ አስቀመጠቻት። ለካስ ይሄ ሁሉ ጥንቃቄ ያስፈ
ለገው ያለ ምክንያት አልነበረም። አንድም የአውቶቡሱ ገንዘብ
ተቀባይ እኔን አይቶ ገንዘብ እንዳያስከፍላት ሲሆን ሌላው ወደ
አሥመራ ይዛኝ መሄዷን ሌሎች ሰዎች እንዳያዩ በመስጋት
ነበር።

አየር አጥሮኝ ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ ማለት ጀመረ! እፍን
ባለው በዚያ አውቶቡስ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ በሕይወት
እንደምቆይ በማሰብ ጨነቀኝ። እንደምንም ብሎ ከሁለት ሰዓት
ጉዞ በኋላ ከመጨረሻው የመውረጃ ሥፍራችን አሥመራ
ከተማ ደረስን። ልክ ከመኪናው እንደወረድኩ አፈፍ አድርጋ
ከብብቷ ስር ከታኝ መጓዝ ጀመርን። ይሄንን ያደረገችው እዚ
ህም ቢሆን ሌላ ሰው እንዳያየኝ በመስጋት ነበር።

ከተማውን ቀደም ሲል ስለምታውቀው ግርግር ያልበዛበ
ትን መንገድ በመምረጥ ጥቂት እንደሄድን የሕዝብ እይታ



የሚቀንስበት አካባቢ ስንደርስ ልጇን በአንቀልባ ካሳዘለችኝ
በኋላ በአንድ እጇ ያንጠለጠለችውን ዕቃ ጭንቅላቴ ላይ
አሸከማኝ ለጊዜው ከምናርፍበት የአንድ የዘመዷ ቤት
ደረስን።

የምትኖርበት ቤት እስከምትከራይ ድረስም አራት ወር
ሙሉ ለእሷም ሆነ በእንግድነት ለተቀበሉን ሰዎች አገልጋይ
ሆኜ ማሳለፍ ነበረብኝ። ቀኑን ሙሉ ያለ እረፍት ስሰራ እው
ላለሁ። ከቤተሰብና ከዘመድ እርቄ በመሄዴም «መድረሻ
ቢስ» የሚለው ቃል እንደስሜ ሁሉ መጠሪያዬ ሆነ። ታዲያ
የፈለገው ነገር ቢፈጠር ዕቃ እንድገዛ አትልከኝም። ምክንያ
ቱም የምታውቀው ሰው በድንገት አግኝታ ልትኮበልል ትችላ
ለች በሚል ሥጋት ሁሌም እንደጠረጠረች ነው።

ያ የማትፈልገው ነገር መከሰቱ ግን አልቀረም። ሳታስ
በው በድንገተኛ በሽታ አልጋ ላይ መዋል ግድ ሆነባት። ያለ
ውድ በግዷታም ወደ ገበያ በመሄድ አንዳንድ እቃዎችን እንድ
ገዛ ላከችኝ። እኔም ስጠብቀው የነበረ አጋጣሚ በመሆኑ ገና
ገበያው መሀል ከመድረሴ ከአንድ ሱቅ ወደ ሌላው እየሮጥኩ
ከትውልድ መንደሬ የመጡ ሰዎች በከተማው ውስጥ
ስለመኖራቸው መጠየቅ ጀመርኩ።

እግዚአብሔር አሁንም ከእኔ አልተለየምና አንዲት አክ
ስቴ በዚሁ ከተማ እንደምትኖር ልደርስበት ቻልኩ።

በጉስቁልናዬ ልባቸው የተነካና አንዳንዶችም አክስቴ ዘንድ በመሄድ ሌላው ቀርቶ ትምህርት እንኳን መማር እንደምችል ነገሩኝ። ልቤም በደስታ ተሞልታ ወደ አሳዳሪዬ ቤት ሳልመለስ በዚያው አክስቴ አለች ወደተባለበት አቅጣጫ አመራሁ።

ቢሆንም አልፎ አልፎ ጠቅ፣ የሚያደርገኝ የጥርጣሬ መንፈስ ሰውነቴን ይወረኛል። የገዛ አባቴ ጨክኖ ያባረረኝን አክስት የምትባለው ሴት ደስ ብሏት እጆቿን ዘርግታ ትቀበለኝ ይሆን? የሚል ስጋት አናወዘኝ። ቢሆንም እንዳገኘኋት ያደረገችልኝ አቀባበል ሞቅ ያለ በመሆኑ ተስፋዬ ለምልሞ ነበር፤ ግን የትምህርት ጉዳይ ሲነሳ ሁሉንም ልጆቿን በማስተማር ላይ ስለሆነች እኔን ከእነሱ ጋር ደርቦ ማስተማር እንደሚከብዳትና እንደማትችል እቅጩን ገለጸችልኝ። ከእርሷ ጋር ለመኖር ከፈለኩ የቤት ውስጥ ሥራ እየሰራሁ መኖር እንደምችል ነገረችኝ። እኔም ምንም ምርጫ ስላልነበረኝ በዚሁ ተስማምቼ ቀን መግፋት ጀመርኩ።

ያ እድል ፈንታዬን የተጠናወተው የስድስት ወር አዚም እዚህም አለቀቀኝም። በተገዛልኝ አንድ ቀሚስ፣ በምበላው ምግብና በማድርበት መኝታ ብቻ ለስድስት ወር ጉልበቴን ገበርኩ።

እያደር ከተማውን እየተለማመድኩት በሄድኩ ቁጥር ከሰዎች ጋር የነበረኝ የግንኙነት አድማስም እየሰፋ ሄደ። ቀስ በቀስም ከሌላ ሰው ቤት ለመቀጠር ሥራ ማፈላለግ ጀመርኩ። ምኞቴም ተሳክቶ አንድ ቤተሰብ ውስጥ ሥራ አገኘሁ።



## ምዕራፍ:- 5

## የነፍሴ ዝማሬ:

«አምላኬን በዝማሬ አመሰግነዋለሁ፣
እንባዬን ከፊቴ ጠርጓልና።
በሀዘንም ምትክ ደስታን አለበሰኝ
እግዚአብሄር አባቴ ነውና።
ከእኔ ምን ጊዜም አይርቅምና
በተኩላዎች መካከል እንኳን
– ብተኛ አይነኩኝም።
በሕመም የተጐዳው ጐኔንም ይጠግናል
ዝቅ ዝቅ ያለው ራሴን ያቀናል
እግዚአብሔር አባቴ ነው
– ለብቻዬ አይተወኝም»

የምሄድበት ዘመድም ሆነ የምጠለልበት ቦታ የሌለኝ ብሆንም በተቀጠርኩበት ቤት ለጥቂት ወራት ካገለገልኩ በኋላ መንስኤው ያልታወቀ ሕመም ስላደረብኝ ስራዬን በግዴታ ለማቋረጥ ተገደድኩ። መንገድ ለመንገድ ስንከራተት መዋልና ማደርም ግድ ሆነብኝ። በላዬ ላይ ከለበስኳት አንዲት ቀሚስና

ለብሻት ከምተኛት የነተበች የብርድ ልብስ በቀር በዚች ምድር ላይ ምንም ንብረት አልነበረኝም።

የእኔ ብጤዎች የጐዳና ሴቶችና ወንዶች ብዙ በመሆናቸው እምብዛም ለብቸኝነት አልተጋለጥኩም። ከፉኛ በበሽታው ስለተጠቃሁም ባለኝና በሌለኝ አቅም እየተንከላወስኩ ከመንገደኞች ላይ እርዳታ እለምናለሁ። አልፎ አልፎ ጉልበቴ ጠንከር ሲልም በየቤቱ እየተዘዋወርኩ ቁራሽ እንጀራ እመፀወታለሁ። በዚህ አጋጣሚ ልገልጸው የምፈልገው የእርዳታ እጃቸውን የሚዘረጉልኝ ሀብታምና ከበርቴዎች ሳይሆኑ ከእኔ በመጠኑ ሻል ያሉት ምስኪኖች መሆናቸውን ነው።

የቱንም ያህል ችግርና መከራ ይፈራረቅብኝ እንጂ ሙሉ እምነቴንና ጽናቴን በእግዚአብሔር ላይ ከማሳረፍ ቅንጣት እንኳን አላፈገፈኩም። በየጐዳናው በመንከራተትና በየግንቡ ሥር በማደር ጥቂት ወራትን ካሣለፍኩ በኋላ ወባ አለዚያም የሳንባ በሽታ ይሆናል ብዬ የምገምተው በሽታዬ በመጠኑም ቢሆን የመሻል ምልክት አሳየኝ።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለሁ መጐሳቆሌን አይታ ያዘነችልኝ አንዲት ሴት ስራ ለመቀጠር መፈለጌንና አለመፈለጌን ጠየቀችኝ። እኔም ፍቃደኛ መሆኔን በታላቅ ጉጉት ገለጽኩላት።

የሴትየዋ መኖሪያ ከቀይ ባሕር አጠገብ በምትገኘው ምጽዋ ወደብ ነበርና ጉዞዬን ከእሷው ጋር ወደዚያው አቀናሁ።



የከተማዋ ዋና ንግድ መርከበኞችን በማስተናገድ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን እሷም የአነስተኛ መጠጥ ቤት ባለቤት ነበረች። የእኔን አይነቷን ጐስቋላና ጐዳና ላይ የወደቀችን ሴት፡ በብዙ ነገር የተጐዳሁና መጠለያ ማግኘት ብርቅ የሆነብኝን እኔን መምረጧ ለስራዋ ታዛዥና ረዳት እንደምሆናት መተማመኛ ሆኗት ነበር። ለእኔም ቢሆን ከአሥመራ ጐዳናዎች ተላቅቄ ወደ ሌላ ከተማ መሄዴ ትልቅ እፎይታ ሰጥቶኛል።

ንግድ ቤቷም ከአንድ ቤተክርስቲያን በስተጀርባ ስለነበር በገባሁና በወጣሁ ቁጥር እረኛዬ ከሆነው አምላኬ እርዳታውን ለመጠየቅና ስለሚያደርግልኝ ሁሉ ተመስገን እንድለውም አስችሎኛል። በዚህ ባልገመትኩት መንገድም ከወደኩበት ትቢያ ላይ ስላነሳኝ ለባዘነች ነፍሴ መጽናኛ የሆናትን የነፍሴን ዝማሬ:

«እንባዬን ከፊቴ ጠርጓልና
በሐዘንም ምትክ ደስታን አላብሶኛል
እግዚአብሔር አባቴ ነው
ከእኔ ምን ግዜም አይርቅም...» እያልኩ
እዘምርለታለሁ።

የምጽዋ ቆይታዬም ከሶስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፈጣን የሆነ ለውጥ በአካሌም፡ ሆነ በጤናዬ ላይ ማስከተል ጀመረ። ግን ይሄ የደስታዬ ጊዜ ብዙም ሳይቆይ በሌላ ፈተና

ላይ ወደቅሁ። ፊቷን የመለሠችልኝ ሕይወትና በሰላም ያሳለፍኩት ሌሊት በአንድ ያልጠበኩት ጠዋት ተመሰቃቀለ። በዚያ በተረገመ ንጋት አንድ የማላውቀው ሰው እየተንገዳገደ በቀጠታ ወደ እኔ መጣ። እኔም ሁኔታውን በግራሞት እየተመለከትኩት በዚያ ጠዋት እንዴትና ምን ጊዜ ጠጥቶ ሊሰክር እንደቻለ እያሰብኩ አመጣጡ ስላስፈራኝ ደንግጬ ቆምኩ።

ወዲያውም ተንደርድሮ በመምጣት በእጄ ላይ የያዝኩትን ትንሽ የገንዘብ ቦርሳ ለመቀማት ክንዴን ጠምዝዞ ከአስፋልት ላይ ዘረረኝ፡ ሕሊናዬን ስለሳትኩም ከዚያ በኋላ የሆነውን ሁሉ ማስታወስ ተሳነኝ። በመጨረሻም እራሴን ሆስፒታል ውስጥ ተኝቼ አገኘሁት።

የተፈጠረውን ሁኔታ ለማወቅ በአጠገቤ ቆሞ የነበረውን ዶክተር ስጠይቀው በአደጋ ሳቢያ የአጥንት ስብራት ስለደ ረሰብኝ ከዚያው ቆይቼ መታከም እንዳለብኝም ተነገረኝ። እን ደተባልኩትም የደረሰብኝ ጉዳት ከባድ በመሆኑ ለስድስት ወራት በሆስፒታል ውስጥ እንክብካቤ እየተደረገልኝ ቆየሁ።

ይሄም ሁኔታ ለእኔ ጨርሶም ያልተጠበቀ አጋጣሚ ፈጠ ረልኝ። እንደ ልቤ እመገባለሁ፡ በሳል አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋር በተለያዩ ርዕሶች ላይ እወያያለሁ። በአጠቃላይ ሥጋ ዊም ሆነ መንፈሣዊ መታደስን አገኘሁ።



ሆኖም እነኛ ስድስት ወራቶች ተጠናቀው ከሆስፒታሉ ስሰናበት ውስጣዊ መንፈሴም ሆነ ውጫዊ አካሌ በመረር ሐዘ ንና ቅሬታ ተናጠ። ቢሆንም እንደፈራሁት ሳይሆን ከሆስ ፒታል ወጥቼ ብዙም ሳልቆይ አጋጣሚ ሆነና ከአንድ ባለ ፀጋ ቤት በቤት ሰራተኛነት ተቀጥሬ መስራት ጀመርኩ።

ጊዜው የምጽዋ ከተማ በሞቃት አየር የምትፈተንበት ወቅት ነበር። ታዲያ ይህን የምጽዋ ወበቅ ለመሸሽና አሥመራ ውስጥ ለማሳለፍ ያለሁባቸው ቤተሰቦች በአንድ መኪና ውስጥ ተሰባስበን ጉዞ ጀመርን። ግን አንድ አስደንጋጭ ሁኔታ በመሃል ተፈጠረ።

ወጣ ገባውንና ጠመዝማዛውን መንገድ ገና ሳናገባድድ ጥቂት መንገድ እንደተጓዝን መኪናችን ከድልድይ ጋር በመ ጋጨት ተገለበጠች። ምንም እንኳን የቤተሰቡ አባላት በተፈ ጠረው አደጋ የከፋ ጉዳት ባይደርስባቸውም እኔ ግን እግሬ በመሰበሩ አሁንም ቤቴ እየሆነ ለመጣው ሆስፒታል ተዳረግኩ።

በሆስፒታልም ውስጥ ከፍተኛ እርዳታ ተደረጐልኝ የአጥ ንት ስብራቴ ቢስተካከልም ቁስሉ ግን ከመዳን ይልቅ እያመ ረቀዘ በማስቸገሩ ሐኪሞች እግሬን ለመቁረጥ ስለማቀዳቸው ደረስኩበት ይሄን ስሰማ የወደፊት ዕድሌንም ማሰብ ጀመርኩ።

ስለዚህ እግሬን አጥቼ ወደ ባሰ ጨለማ ከመግባቴ በፊት የሚደርስብኝን ሁሉ ለመጋፈጥ ሆስፒታሉን ጥዬ ለመውጣት ተገደድኩ።

ወደ መንደር ወጌሻም በመሄድ በአገር ባህል መድሐኒት መረዳት ጀመርኩ። ባጭር ጊዜም ውስጥ ከሚሰማኝ የማያቋርጥ ስቃይ እፎይታ አገኘሁ። ቁስሉም እየዳነ መሄድ በመጀመሩ በመጨረሻ ሙሉ በሙሉ ጤንነት ስለተሰማኝና ያለችግር መራመድ በመቻሌ ቀሪ ሕይወቴን ለመምራት ከአንዲት ሴትኛ አዳሪ ቤት ተቀጠርኩ።



## ምዕራፍ :- 6

## የክብረ ንጽህናዬ መደፈር።

አሁን እድሜዬ ከአስር ዓመት ዘለል ብሎዋል። በሀገራችን ባህልና ወግ መሰረት ለጋብቻ የምመጥን ልሁን እንጂ ያለ ቤተሰቤ ፈቃድ ማንም አስገድዶ ሊደፍረኝ እንደማይችል በማመን ሁሌም የልብ ልብ ይሰማኛል፣ ስጋትም ይርቀኛል።

አሳዳሪዬ የለየላት ሴሰኛ ነች። ሁሌም ከስሯ መለየት የማይሆንለት አንድ ሰው አመለካከቱ አንድም ጊዜ ደስ ብሎኝ አያውቅም። መቼውንም ቢሆን ስገባና ስወጣ፣ ስቀመጥም ስነሳ ዓይኑ ከእኔ ላይ አይለይም። በዚህ ሁኔታው መንፈሴ ይረበሻል፣ ፍራቻና ጥርጣሬ በውስጤ ይተራመሳል።

አንድ ቀን ሴትየዋ ባልነበረችበት ሰዓት አጋጣሚውን ጠብቆ ያ ሰው እቤት መጣ። በድንገት አፌን በጨርቅ አፍኖ እግርና እጄን አስሮኝ በጓሮ በር ተሸክሞኝ ወጣ። እቤቱ ካደረሰኝ በኋላም ያሰረኝን እግሬንና እጄን በመፍታት አንዳችም ድምጽ እንዳላሰማ አስጠንቅቆ አፌ ላይ አስሮት የነበረውን ጨርቅ አወለቀልኝ። እምቢ ካልኩትም ጉዳት ሊያደርስብኝ ይችላል በሚል ስጋት ተጨነኩ። እሱ ግን ባለና በሌለ አቅሙ ሁሉ ሊያዝናናኝና ሊያስደስተኝ ቢሞክርም እኔ ፈቃደኛ

አልሆንኩለትም። ለተከታታይ አራት ቀናት አስገድዶ ሊደፍረኝ ቢሞክርም ባለኝ አቅም ሁሉ እየታገልኩ አስቸገርኩት። በአምስተኛው ቀን ግን ተሸነፍኩ። እንዳልንቀሳቀስ እጄና እግሬን አስሮ አፌንም አፍኖ ከብረ ንጸህናዬን ደፈረው።

ይሄን መሰሉ ግፍ በግዳጅና በድብደባ ከተፈፀመብኝ በኋላ ሕሊናዬን ሳትኩ፤ በተከታዩ ቀንም ሰውነቴ ተሳስሮ መንቀሳቀስ ስለአቃተኝ እቤቱ ውስጥ እንዳልሞትበት በመስጋት ብቻ ሆስፒታል ሊወስደኝ ተገደደ፤ ቢሆንም ሆስፒታል ውስጥ ስለ በሽታዬ መንስኤ ለሐኪሞቹ የነገራቸው እራሱን ከተጠያቂነት ለማውጣት የሚያስችለውን አሳፋሪ ዓይነት ውሸት ነበር። ይሄውም እኔን የጉዳና ተዳዳሪ አስመስሎ በማቅረብና በመንገድ ዳር ተኝቼ ሳቃስት በማግኘቱ እኔን ለመርዳት በሀዘኔታ ወደ ሆስፒታል ሊያመጣኝ እንደቻለ አድርጎ ነበር የተናገረው።

ሁለት የስቃይ ሳምንታት በሆስፒታል ውስጥ ካሳለፍኩኝ በኋላ በሐኪሞች ትዕዛዝ እንድወጣ በመደረጉ ለጊዜው ሌላ መግቢያ ስላሌለኝ አሁንም ወደ ሴትየዋ ቤት ለመሄድ ተገደድኩ። እሷም በዛ በግፈኛ ሰው ድርጊት ሳቢያ ትከሰኛለች ብላ ስለፈራች ተመልሼ ወደ ቤቷ እንዳልገባ ከለከለችኝ።

በመጨረሻም መጠጊያና መግቢያ በማጣቴ እንደመሰሎቼ ወጣት ሴቶች ሁሉ በይፋ በመጠጥ ቤት አሻሻጭነት ተቀጠርኩ። አሰሪዬም ደህና ገበያ እንድስብላት ለአለባበሴና ለአመጋገቤ ጥንቃቄ ታደርግልኝ ጀመር። በምትሄድበት ቦታ ሁሉ ተከትያት እንድሄድ በየሆቴልና መናፈሻ ስፍራም አብሬያት እንድዞር በማድረግ ወንዶችን በፈገግታ እንድቀርብና በሚቻለኝ ሁሉ እንዳግባባቸው ዕለት በዕለት ማበረታታቱን ቀጠለች። እኔም ስጋዬን እንደ ሸቀጥ ለማንም እየሸጥኩ ማደሩን እየተለማመድኩት መጣሁ። የመጠጥ ቤቱንም ኑሮ ለመድኩት።

የቤቱም ገበያ እየሞቀ በመሄዱ ልብስና ጫማዬን እንድቀይር ከአሰሪዬ ግፊትና ማበረታቻም አልተነፈገኝም፤ እንዲያውም ይባስ ብላ ለአጭር ጊዜ የዝሙት ፍላጎት ብቻ የሚመጡ ሰዎችን እንዳስተናግድ ልዩ ክፍል ሁሉ አዘጋጀችልኝ። በዚያን ወቅት ባይበዛም በመጠኑ መጠጡንም መቀማመስ ጀምሬ ነበር። ይሄም ለሚሰማኝ ሀፍረትና ካለ ዕድሜዬ እየፈፀምኩት ላለው ያላሰለሰ ሥጋዊ ግንኙነት በማደንዘዣነት ረድቶኛል።

ባለቤቲቱም ደህና የገቢ ምንጭ ስለሆንኩላት እያንዳንዱን እንቅስቃሴዬን ትከታተል ነበር። በተለይ ቡና ቤቱን በቋሚነት የሚያዘወትሩት የባሕር ኃይል ሰራዊት አባላት ነበሩ። ታዲያ በዚህ ሥራዬ አጋጣሚ ከአንድ ወጣት የባህር ኃይልአባል ጋር ፍቅር ብጤ ይሞካከረኝ ጀመር። ለእኔ ያለው አመለካከትም ለየት ያለና ርህራሄ ያልተለየው በመሆኑ ይበልጥ መቀራረብና ዕለት በዕለት መገናኘት ቀጠልን።

አንድ ጊዜ በአንድ የሳምንቱ መጨረሻ ቀን ከከተማው ወጥተን ለመናፈስ በምንጓዝበት ወቅት ያሽከረክራት የነበረች

ጂፕ መኪና ወደ ገደል በመገልበጧ እሱ ወዲያው ሲሞት እኔ ግን ተረፍኩኝ። ምንም እንኳን ከሞት ብተርፍም በደረሰብኝ ጉዳት ምክንያት ከዚያው ከለመድኩት ሆስፒታል ተወስጄ ከሁለት ወር በላይ ከፍተኛ የሕክምና እርዳታ እየተደረገልኝ ቆየሁ። ሆኖም የሐኪሞቹ አቀባበል እንደ ቀድሞው አልነበረም። እኔ ላይ የመሰልቸት ስሜት ይታይባቸዋል። ስለዚህ ነበር ገና ከሕመሜ ሙሉ ለሙሉ ሳላገግም ከሆስፒታሉ እንድወጣ የተደረገው ።

ምንም እንኳን ለስጋዊ ስሜቴ ተሸንፌ ሳይሆን ለመኖር በማደርገው ትግል በዝሙት ሥራ ላይ ብውልም በአምላኬ ላይ ጽኑ እምነት አለኝ። ይሁንና በጓደኞቼ ግፊት ለጤናዬ መታወክ መፍትሄ ይገኛል በሚል ምኞት ወደ ጠንቋይና አስማተኛ ቤት ለመሄድ ወሰንኩ።

እግዚአብሔር ግን ከዚህ ድርጊቴ እንድቆጠብ ከአንዴም በላይ ሁለት ሶስት ጊዜ በተደጋጋሚ በሕልሜ አስጠንቅቆኛል። እኔ ግን ከበሽታዬ ቶሎ ለመዳን ባለኝ ፍላጐት የአምላኬን ትዕዛዝ ተጋፋሁኝ። ቀስ በቀስ እራሴንም የባዕድ አምልኮ ተገዢ አድርጌ አረከስኩት። ተስፋዬና መጠለያዬ የምለውን ጌታዬንም አሳዘንኩት። የዚህ ሃጢአቴም መዘዙ ለተከታዮቹ ሰባት ዓመታት የሥቃይ ሕይወትን እንድመራ ዳረገኝ።



# ምዕራፍ : 7

## የባዕድ አምልኮ ወጥመድ

ቤቱ በሚሰነፍጥ ሽታ የታጠነ በመሆኑና በየግርግዳው ላይ እዛም እዛም የተንጠለጠለው ጨሌና ድሪ ከፍተኛ ፍርሃት ለቀቀብኝ በሌላ በኩልም ከእግዚአብሔር ዘንድ በሕልሜ የተነገረኝ የ«አትሂጂ»ን ማስጠንቀቂያ ቃል በመጣሴ ልቤ በጭንቀት ተሞልቷል።

ጓደኞቼ የመሸከም ያህል ነው እጄን ይዘው እየጐተቱና እየገፉ ያስገቡኝ። የእኔ ተራ ደርሶ አዋቂ የተባለው ሰው የሰጠኝን ትዕዛዞች ሁሉ አሁን ሳስባቸው በእጅጉ ይገርሙኛል። መገረምም ብቻ ሳይሆን የሚዘገንንና አሳፋሪም ነበር። የተለያዩ ቀለም ያላቸውን በጐችና ዶሮዎች አርጂ ደማቸውን እንድጠጣና በደማቸው ሰውነቴን እንድታጠብ ጭምር ትዕዛዝ ያዘለ ምክር ለገሡኝ።

ከሕመሜና ከችግሬ ለመገላገል በመኳኳት የታዘዝኩትን ሁሉ ለመፈፀም ቃል ገብቼ ለተደረገልኝ ሁሉ ገንዘብ መክፈል ብቻ ሳይሆን ከእሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመፈፀም ወደ መኖሪያ ቤቴ ተመለስኩ።

በመጨረሻም የሕመሜ መንስኤ ዛር መሆኑ ተገልጾልኝ በሰዎች መሃል መጨፈሩንና ማጓራቱን ተያያዝኩት። ማጓራቱ

አብቅቶም ከመሬት ላይ ተዘርሬ ስወድቅ በእጣን ጭስ እንድታጠንና ደም እንዲረጭብኝ ይደረጋል።

በእኔ ላይ የሰፈረው የዛር መንፈስ እጅግ ከባድና ትንቢት ሊናገር የሚችል ስለመሆኑ በጠንቋዩ ምስክርነት ስለተሰጠኝ ትልቅ ዝናንም አተረፈልኝ።በዚህም ለጊዜውም ቢሆን መኩራራቴ አልቀረም ነበር። ይህም ሆኖ ውስጤን የሚሰማኝ አንድ የቅሬታ ስሜት ሰላም ነሳኝ። እሱም በእግዚአብሔር የማምንና በጥበቃውም የምመካ ሆኜ ለጠንቋይና ለርኩስ መንፈስ መስገዱ የቱን ያህል ከቀናው መንገድ ማፈንገጤ ነበር። ሆኖም የጥንቱን ፍቅሩን እንዲያድስልኝ አምላኬን አጥብቄ ተማፀንኩት። ወደ ውድቀትና አዘቅት ከሚወስደው የተሳሳተ ጐዳና መልሶ በቀና መንገድ ይመራኝም ዘንድ አለማቋረጥ መጸለይን ተያያዝኩት።

በዚህን ጊዜ ስሜን በመልካም የሚያነሳው ማንም ሰው አልነበረም። ያቺ ጠንቋይና ያቺ ዛራም የሚለው ቃል መጠሪያዬ ሆነ። አንዳንድ የሚያውቁኝ ሰዎች ገና ከርቀት እኔን ሲያዩ መንገድ ለውጠው ይሄዳሉ፣ ወይም ፊታቸውን ያዞራሉ። እንግዲህ ለዚህ መሰሉ አሳዛኝና ምስቅልቅሉ ለወጣ ሕይወት የተዳረኩት ገና በአሥራ ሰስት ዓመት ዕድሜዬ ነው።

ከጠንቋዩ ተጽዕኖ ሙሉ በሙሉ እስከላቀቅ ድረስ ያወጣሁት የገንዘብም ሆነ የምራል ኪሣራ በቀላሉ የሚገመት



አልነበረም። ማንኛውንም አድርጊ የተባልኩትን ነገር ሁሉ (የግብረ ሥጋ ግንኙነትን) ማሟላት ነበረብኝ ያን ካላደረኩ የሚጠብቀኝ ስቃይ አስከፊነቱ ከበፊቱ የባሰ እንደሚሆን ያስጠነቅቀኛል። ይሄ ሁኔታ ደግሞ በኑሮዬና ሰርቼ በማገኛት ገንዘብ ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጠረብኝ፤ ቢሆንም መላቀቁ እንዲህ በዋዛ የሚታይና በቀላሉ የሚፈፀም አልነበረም

በተደጋጋሚ የሞከርኳቸው የግል ጥረቶቼ ከምንም እንደ ማያድኑኝም በመረዳቴ ወደ አምላኬ ተመልሼ ከዚህ ምድራዊ ሲኦል እንዲገላግለኝ የሙጥኝ አልኩት። እግዚአብሄርም እምባዬን አበሰልኝ በውስጤ የነበረውን የሰይጣን አሰራርም ከእኔ ቆርጦ ጣለው ዳግመኛም ወደ ጠንቋይ ቤት ላለመሄድ ቁርጥ ውሳኔ ላይ ደረስኩ።

# ምዕራፍ :- 8

## ከሙታን ያልተሻለ ሕይወት

«አሁንም አምላኬ – እንደ ጥንቱ አድሰኝ
በመንፈስ በአካልም – የበረታሁ አርገኝ።
አንተን «ለመመስከር» – ጽናት ብርታት ስጠኝ...»

በጉስቁልናና፣ በሕመም የተበተበተው ሰውነቴ በቀላሉ ሊያገግም አልቻለም እንደውም አንዳንድ ጊዜ ሕሊናዬን እስከመሳትና እራሴንም እስከ መዘንጋት እደርሳለሁ። ይህም ሆኖ እግዚአብሔር ፊቱን እንደመለሰልኝ እርግጠኛ ነበርኩ።

ሌላው ችግሬ የዛሬዋን እስትንፋሴን ለነገ ለማሳደር ያለኝ አማራጭ አንድና ብቸኛ መሆኑ ነበር። ስለዚህም እንደ ቀድሞው በአሻሻጭነት የቡና ቤት ሥራዬን ቀጠልኩ።

በሌላ በኩል በማያቋርጥ የሆድ ቁርጠትና ከማህፀኔ ባለመገታት በሚፈስ ደም እሰቃያለሁ። ያም ብቻ አይደለም ሆዴም የደረሰች ነፍሰ ጡር ያህል ገፍቷል። ልክ ሕይወት ያለው ጽንስ የተሸከምኩ ይመስል የሚገላበጥ ነገር ይሰማኛል። ይሄን ችግሬን ለሐኪም ከማማከር ውጭ ወደ የትኛውም ባህለኛ ሐኪም ወይም ወደ ሌላ ላለመሄድ ወሰንኩ። ይሁን



እንጂ ሆስፒታል ሊያስተኛኝም ሆነ ተመርምሬ ለሚታዘዝልኝ መድሐኒት መግዣ የሚሆን ገንዘብ ጨርሶ አልነበረኝም።

ስለዚህም አንድ ሃሳብ መጣልኝ። የነበረኝንም የመጨረሻ አማራጭ ለመውሰድ ወሰንኩ። በተቻለ መጠን ወደ ሆስፒታሉ ክልል እንደደረስኩ በማይታሰብ ፍጥነት ተንደርድሬ በመሮጥ ከሆስፒታሉል መግቢያ በር ጋር ባለ በሌለ ሃይሌ ተላትሜ እየጮህኩ ተዘረርኩ:- ወዲያው በሁኔታው የተደናገጡት የሆስፒታሉ ሠራተኞች አንስተው ድንገተኛ ክፍል አስገቡኝ። አስፈላጊው ምርመራ ሁሉ ተደረገልኝ። ቢሆንም የሕመሜን ምንነትና መንስኤ ለመረዳት ችግር ስለገጠማቸው ሐኪሞቹ ተቸገሩ። ለረጅም ጊዜ የተለያየ ምርመራ ቢያደርጉልኝም ስለሚያስፈልገኝ ሕክምና ስምምነት ላይ መድረስ ተሳናቸው።

ከፊሎቹ የቀዶ ሕክምና እንደሚያስፈልገኝ ሲያምኑበት ሌሎቹ ግን ሕመሜን እንደ ቀላል በመውሰድ አልጋ ይዤ መታከም እንደማይገባኝ ይከራከሩ ጀመር።

የነበረኝ ብቸኛው መጽናኛ አምላኬ ብቻ ነው። በአንድ በኩል ከሕመሜ እንዲገላግለኝ ስለምነው በሌላበኩል ከሆስፒታል እንዳያስወጡኝ ልባቸውን እንዲያራራልኝ እነዘንዘዋለሁ። በሆዴ ውስጥ የተሸከምኩትንም ያልታወቀ ጉድ በማስወገዱ እንዲገላግለኝና ጤናማ ሕይወት እንዲሰጠኝ እንደ ሕፃንነት ዘመኔም በንፁህ ሕሊና እንዳመልከው አዘውትሬ

« አሁንም ፣ አምላኬ
– እንደ ጥንቱ አድሰኝ
በመንፈስ ፣ በአካል:-

የጠራሁ አድርገኝ።

እያልኩ ወደ እሱ አነባለሁ።

በሆስፒታል ውስጥ ቆይታዬ ሁኔታዬ እያደር እየተባባሰ ሄደ። በኋላም ያደረብኝ አካላዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ቀውስ መሆኑን ሐኪሞቹ ተረዱልኝ። የቀዶ ሕክምና እንዲደረግ ልኝም ተወሰነ። ቢሆንም ሕክምናው ከመጀመሩ በፊት ለሚደ ርስብኝ አደጋ መስማማቴን በፊርማዬ ማረጋገጥ ነበረብኝ። ይሁን እንጂ መጻፍም ሆነ ማንበብ ስለማልችል እግዚአብሔር እንደመራኝ ለፊርማ የተሰጠኝ ወረቀት ላይ ጫጫርኩበት። ከዛ በኋላም አስፈላጊው የቀዶ ሕክምና ተካሄደ።

እንደተነገረኝ ከሆነ ከቀዶ ጥገና በኋላ ትንፋሼ ሙሉ በሙሉ በመቋረጡ እንደ ሞትኩ ተቆጥሮ ወደ ሬሣ ማስቀመጫ ክፍል ተወስጄ ነበረ። ሆኖም ሁሉንም ባስገረመ ሁኔታ እንደገና ነፍስ ዘርቼ ወደ ማገገሚያው ክፍል ተዛወርኩ። ይሄን ጊዜ ነው ለጥፋቴ ተመጣጣኝ ቅጣት መቀበሌ መሆኑን ያመንኩበት። ይሄ ሁሉ በገዛ እጄ ያመጣሁት ጣጣ ነው፤ በዚያ ጠንቋይ ባላምንና ለእርኩሳን መናፍስት ደም ባልገብር፤ መድሐኒት ነው እያለ የሚሰጠኝን ሁሉ ባልጋት ኖሮ ሆዴም ወሯ እንደገባ እርጉዝ ሴት ባላበጠም ነበር።

ከሆዴ ውስጥ ያወጡትን ነገሮች አሳዩኝ። ያንን ወጣ የተባለውን ነገር ሳይ እራሴን መቆጣጠር አቃተኝ። ማንስ ቢሆን ያምናል? ማንስ ያንን ጉድ ተመልክቶ እራሱን መቆጣጠር ይችላል? በማህፀኔ ውስጥ ከእባብና አይጥ ከእንቁላልና ድንጋይ በተጨማሪ የቅጠላ ቅጠልና የፍራፍሬ ቁርጥራጭ ተሸክሜ ነበር ብል ማንስ እውነት ይለኛል?



በህክምናው ታሪክ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ የማይታወቅ ትንግርት በእኔ ላይ በመፈፀሙ ሐኪሞቹ እጅግ ግራ ተጋብተው ነበር። ቀዶ ጥገናውን በችሎታቸው ብቻ ሳይሆን በአንድ «ልዩ ተዓምርና ሃይል» ምሪት ያከናወኑት ስለመሆኑም አንዳቸው ሳይሸሽጉ በዝርዝር ተናግረውታል።

የሕመሙ ስቃይና ስሜት ከቀን ወደ ቀን እየተሻለኝ በመሄዱ ከሆስፒታል ወጣሁ። በዚህ ወቅት በእጄ ላይ አንዲት ሣንቲም እንኳን አልነበረኝም። ከእንግዲህ ወዲያ አሥመራ ውስጥ የመቆየት ፍላጐቴም ተሟጧል፤ ስለዚህም በሆነው አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅሜ ለመጓጓዣ የሚሆነኝን ገንዘብ ማሰባሰብና ወደ ትውልድ ሐገሬ ዋና ከተማ መቀሌ መመለስ ብቻ ነው።

መንገድ ለመንገድና በየቤቱም በመዟዟር ለመጓጓዣ የሚሆነኝን ገንዘብ መለመን ቀጠልኩ፤ መጓዝ ያለብኝም በአውሮፕላን ብቻ ነው። ያ ካልሆነ ግን ገና ያልጠገገውና በቀዶ ጥገና የተተለተለ ሆዴ በቀላሉ የመተርተር ዕድሉ ሰፊ ነበር። ያሰብኩትም ተሳካና በሰላም መቀሌ ደረስኩ። ከመጓጓዣ በተረፈኝም ገንዘብ ከተማው መሃል አንዲት አረቄ መቸርቸሪያ ንግድ ብጤ ከፈትኩኝ።

በወቅቱ በአካባቢው የተፋፋመ ጦርነት እየተካሄደ ስለነበር የከተማው ሕዝብ በየዕለቱ ይባንናል። ያም ሆኖ ግን ሕይወትን እንደ አመጣጡ ከማስተናገድ ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረምና ሁሉም በየፊናው ለመኖር ይንደፋደፋል።

# ምዕራፍ ፡ – 9

## ዳግመኛ መገናኘት

እንዴት አድሪጐ መኖርያ ቤቴን ፈልጐ እንዳገኘው ይገርመኛል። ልክ እንዳየሁት ያደረብኝ ስሜት የተለየ ነበር። ከቤተሰብ ጋር ሊያስታርቀኝ የመጣ መስሎኝም እልህና ንዴት ተናነቀኝ ። ያሳለፍኩትን አስከፊ ውጣ ውረድ ቢያውቅ ምን ይሰማው ይሆን ብዬም አሰብኩ።

ወንድሜ ያገኘኝ የአረቂ ንግዴን ትቼ አንድ ቡና ቤት ውስጥ በአሻሻጭነት ከተቀጠርኩ በኋላ ነው። በዚያ ስራ ላይ በመሰማራቴም ሳይናደድ አልቀረም። ይብሱን በዚያን ጊዜ ሲጋራ አጤስ ስለነበር በዚህም ጭምር ቅር ተሰኝቷል። ለቤተሰቦቼ ያለኝ ፍቅር ሙሉ በሙሉ ከውስጤ ባይሟጠጥም ያለፈው በደላቸው ግን ከሕሊናዩ ሊፋቅ አልቻለም። ለበደላቸው ይቅር ልላቸው እንደሚገባኝ አምናለሁ፡ ግን የእግዚአብሔር ፀጋና ብርታት ሲታከልበት እንጂ በእኔ ሰብአዊ ባህሪ ይቅርታው ከባድና ልቋቋመው የማልችለው ጉምዛዛ ሆነብኝ።

ለካስ ይሄን አቋሜን ለውጦ እግዚአብሔር በሌላ መንገድና አሰራር ተሸናፊ እንድሆንና ዳግመኛ ከቤተሰቦቼ ጋር የምቀራረብበትን መንገድ አዘጋጅቶ ኖርዋል። በዚያው



አጋጣሚ ሌላ ሕመም ስላደረብኝ በወንድሜ አነሳሽነት እንደ ጥንታዊው ባህልና እምነት መሠረት ወደ ጠበል መሄድ ነበረብኝ። ግን ወደዚያ ወደ ተቀደሰ ስፍራ ከመሄዴ በፊት እግዚአብሔር ከበሽታዬ እንዲፈውሰኝ ፈጣሪዬን መለመንና ለእግዚአብሔር ፍቅርና መሃሪነት ስል የበደሉኝን ሁሉ ይቅር ማለት ነበረብኝ። ስለዚህም ለቤተሰቤ ይቅርታ አሻፈረኝ ብሎ ያመፀው ድንጋይ ልቤን እግዚአብሔር ባልጠበኩት መንገድ አፈራረሰው። ፈታው።

ወንድሜም እኔን ፀበሉ ከሚገኝበት ሥፍራ ካደረሰኝ በኋላ ወደ ትውልድ መንደራችን ተመለሠ። ፀበሉም የሚገኘው በጉድጓድ ውስጥ ስለነበር እርቃኔን በመሆን በወገቤ ላይ ገመድ እየታሰረ ወደ ታች ፀበሉ ወደሚፈስበት ጉድጓድ እለቀቅ ነበር። ያም ሆኖ ከፀበሉ አገኛለሁ ብዬ የጠበኩትን ፈውስ ባለማግኘቴ ተስፋዬ እየተሟጠጠ መጣ። ስለዚህም በፀበሉ ከተጠመኩና ከጠጣሁ በኋላ በአካባቢው በሚገኝ ጫካ ውስጥ ብቻዬን መዘዋወር የየዕለት ተግባሬ ሆነ።

አንድ ቀን ታዲያ በአካባቢው ከብት የሚጠብቅ እረኛ በቀጥታ ወደ እኔ በመምጣት በረጋና ትዕዛዝ በታከለበት አንደበት ወደ አሥመራ እንድሄድ ተናገረኝ። ያ ልጅ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ስለመሆኑ ቅንጣት አልተጠራጠርኩም። ስለዚህም ወደ አሥመራ ለመሄድ ልቤ ተነሣሣ።

እግዚአብሔርም ከእኔ ባለመለየቱና ሁልጊዜም ከመከራ እንደሚጠብቀኝ አምናለሁ። ማንኛውም ችግር ሲገጥመኝ

«በርትተሽ እምነትሽን አጠንክሪ

አምላክሽ እግዚአብሔር ከማንኛውም ክፉ ነገር ይጠብቅሻል»

የሚል መልዕክት በጆሮዬ ያቃጭላል። እኔም በዚህ ቃል እበረታለሁ።

ወደ አስመራ ስመለስ ሙሉ በሙሉ ጤነኛ አልነበርኩም በአካልም ሆነ በመንፈሴ የተረጋጋሁ ስላልነበርኩ ፀባዩ ቅብጥብጥ ሆነ። ስለዚህም አዘውትሬ ሐኪሞችጋ መመላለስ ግድ ነበር። በጤናዬ በኩል ያን ያህል መታወክ ገጥሞኝ እያለሁ የአገሪቱ የተናጋ የፀጥታ ሁኔታ መባባስ ይብሱን ስላምና የኅሊና እረፍት ነሳኝ።



# ምዕራፍ :- 10

## ሽሽት:

በየአቅጣጫው የተኩስ እሩምታ ይሰማል፡ ያቺ መግቢያና መውጫዋን አብጠርጥሬ የማውቃት የአሥመራ ከተማ በምጥ ተይዛለች፡ በነፃ አውጪውና በኮሚኒስቱ ወታደ ራዊ መንግስት መካከል እየተካሄደ ያለው ትንቅንቅ ከተማዋን ንጧታል።

እኔም በዚህ አጋጣሚ ነበር ጓደኛዬ ሊዛንና ልጆቿን ለመ ጠየቅ ጉዞ ላይ የነበርኩት። በጉዞዬ አጋጣሚም እየተፈፀመ ያለውን ድርጊት በርቀት ሆኜ ለመመልከት ዕድሉ ገጥሞኛል። ማንኛውም በመንገድ የሚተላለፍ ሰው በመንግስት ወታደሮች እንዲቆም ይደረጋል። እናም ይፈተሻል፡ አልፎም እንዳስ ፈላጊነቱ በጥይት ይደበደባል።

በተለይ አንድ ምሽት በድንገት አካባቢያችንን የተኩስ ድምጽ አተራመሰው። ወዲያው እጅግ የሚሰቀጥጥ የሰዎች ጩኸትና እሮሮ ይሰማ ጀመር። እኛም ከፍርሀታችን የተነሳ ሕፃኗ የሊዛ ልጅ እንዳታለቅስ እያባበልናት ሌሎቹም ምንም አይነት ድምጽ እንዳያሰሙ አስጠነቀቅናቸው። እኛ ዕድለኞች ሆነን ሌሊቱን በዚህ ሁኔታ ብናሳልፍም ከጐረቤቶቻችንን

ብዙዎቹ ግን ንጋት ላይ ከቤት እየተጐተቱ ተገድለው ሜዳ ላይ ተጥለው ነበር። ይሄ ሁኔታም ለተከታታይ አራት ቀናት በመቀጠሉ የምንቀምሰው ምግብም ሆነ ውሃ እስከማጣት ደርሰን ነበር።.የአሁኑ ዙር ግጭት ከመፋፋሙ በፊት እኔና ሊዛ የተዋወቅነው ፍራንክ (እውነተኛ ስሙ አይደለም) የሚባል አሜሪካዊ ሰው ነበር። እጅግ ስለተቀራረብንና ብዙ ጊዜ ስለ አገሪቱ ባህልና ታሪኳንም በተመለከተ አንዳንድ ነገሮች አጫውተነዋል። ታዲያ ያ ሰው ነበር ባልገመትነውና ባልጠበቅነው ወቅት ሕይወታችንን የታደጋት ።

እሱ በዜግነቱ አሜሪካዊ ስለሆነ በማንኛውም ሰዓት ከተማዋን ለቆ የመውጣት መብት አለው። ለሌላው ነዋሪ ግን ከከተማዋ መውጣት ቀርቶ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እንኳን ክልክል ነበር። ይሄ ወዳጃችንም ሊዛን በሚስትነት እኔን በልጅነት አስመዝግቦ የፈቃድ ወረቀት በማውጣት የገንዘብና የጊዜ መስዋዕትነት በመክፈል ከአሥመራ ከተማ ለማስወጣት ረዳን።

ሁለታችንም የአሥመራ ከተማን ለቀን ወደ መቀሌ በአውሮፕላን ለመብረር ወደ አየር ማረፊያው ጉዞ በጀመርንበት ወቅት ያያሁትን በየመንገዱ የነበረ ሬሣ እስከመቼም አልረሳም።

መቀሌም እንደደረስኩ ልክ እንደበፊቱ የአረቄ ንግዴን ጀመርኩ። ከተማ ውስጥ ብዙ ወታደሮች በመኖራቸውም



ንግዴ ጥሩ እንቅስቃሴ ነበረው። ቢሆንም የፀጥታው ሁኔታ እንደ አሥመራ የከፋ ባይሆንም ከዛሬ ነገ ጦርነት ይፈነዳ ይሆናል በሚል ሥጋት መጨነቃችን ግን አልቀረም።

በየጊዜው አዋጅ ይተላለፋል፣ የምግብ እጥረትም ተከሥቷል ከአሥመራ በመቶ ኪሎ ሜትሮች ብንርቅም አመጹ ግን እየተስፋፋ ከተሞችንም ሆነ የዳሩን አገር እያጥለቀለቀው ነው። እናም ንግዴ የቱንም ያህል የደራ ቢሆን የጦርነቱ ጥላ በመቀሌም ላይ እያንዣበበ በመምጣቱ የአሁኑ ብቸኛው ምኞቴና ፍላጐቴ አገር ጥሎ መሰደድ ብቻ ሆነ።

## ክፍል :- 2

## ምዕራፍ : – 11

# የማታለያ ምክንያቶቼ

የመቀሌ ከተማ የፀጥታ ሁኔታ ከመረጋጋት ይልቅ ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ ሄደ። እንደ አሥመራ ከተማ በየመንገዱ ሬሣ ባይረፈረፍም ሰላማዊውን ሰው ሳይቀር እየገደሉ በየ ሥርቻው መጣል በወታደሮች ዘንድ የተለመደ ተግባር ሆኗል። እኔም ወደ አሥመራ የመሄድ እቅድ እንዳለኝ ወሬው እንኳን ቢሰማ በቀጥታ አደጋ እንደሚደርስብኝ አውቀው ነበር።

ያለኝ ብቸኛ አማራጭ ከተማውን በሆነ ዘዴ ማንም ሳያውቅ በሚስጥር ለቆ መውጣት ብቻ ሲሆን በሌላ በኩል የከተማው ዙሪያ ገባ የጦር አውድማ በመሆኑ መንገዱ ሁሉ ተዘግቷል። በማንኛውም ተሽከርካሪ ሾልኮ ለመውጣት ፈጽሞ የማይቻል ነው። ስለዚህም በአየር ለመብረር አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ መክፈል ነበረብኝ።

በሌላ በኩል የይለፍ ፈቃድም ለማግኘት እጅግ አድካሚና አታካች ሆኖብኝ ነበር። ምናልባት ቢያዋጣኝም ባያዋጣኝም በማለት በልክፍት በሽታ በመያዜ አካባቢዬን ሰላም ስለነሳሁና



ማህበራዊ ሕይወቴም ስለተበላሸ አካባቢውን መልቀቅ እፈልጋለሁ የሚል ምክንያት ነበር ለባለስልጣኖቹ ያቀረብኩት። ምክንያቴም ተቀባይነት አግኝቶ የይለፍ ወረቀት ተሰጠኝ።

ምንም እንኳን የስድስት ሰዎች ሒሳብ እንድከፍል ቢደረግም የመቀሌን ከተማ የለቀኩት በሔሊኮብተር ነበረ። በጉዞዬም ላይ ከፍርሃት፣ ከሥጋትና ከሰቀቀን የመገላገያ ጊዜዬ መቃረቡ እየታወቀኝ ደስተኛ ስለነበርኩ በዚያች ሄሊኮብተር ውስጥ አቀማመጤ እንደ አንዲት ልዕልት ተዝናንቼ ነበር። ከንግስት ሳባ ሲወራረድ የመጣ ትውልድ እንዳለኝ በዚያን ወቅት አምኜበት ነበር ብል ማጋነን አይሆንም።

አሥመራ እንደደረስኩ ያረፍኩት ከቀድሞ ጓደኞቼ ቤት ነው። ከጥቂት ቀናት ቆይታም በኋላ ስለሚቀጥለው ዕቅዴ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ጀመርኩ። አሣቤ በዚያች በጦርነት ከምትታመስ አገር እንደምንም ወጥቼ ወደ ሱዳን ለመሰደድ ነው። ነገር ግን ከአሥመራ ወደ ሱዳን መሄድ ቀርቶ ከወረዳ ወደ ወረዳ ለመዘዋወር እንኳን ትልቅ ችግር ነበር። በእያንዳንድ እንቅስቃሴ የይለፍ ወረቀት መያዝ ወሳኝ ነው።

ወደ አሥመራ ፖሊስ ጣቢያ ሳልሰለች በመመላለስ ለሱዳን ድንበር ቅርብ በሆነችው የቱስካኒ መንደር ውስጥ አክስቴ ታማ ጣር ላይ በመሆኗ ሄጄ ልጠይቃት እንደሚገባኝ

አመለከትኩ። አሁንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ፖሊሶቹ ሊፈቅዱልኝ ቻሉ።

የመጓጓዣው ነገር ግን ሌላ ችግር ሆነ። ልክ ከመቀሌ እንደወጣሁት ሁሉ ላደርግ የምችለውን ሁሉ መሞከር ነበረብኝ። ስለዚህም ያለ የሌለ ንብረቴን አሰባስቤ በመሸጥ አንዲት ትንሽ አውሮፕላን በኮንትራት መያዝ ቻልኩ።

ጉዞዋችንን ጀምረን በበረራ ላይ እንዳለን አብራሪውን ሱዳን እንዲያደርሰኝ እንደምንም ላግባባው አስቤ ነበር። ሆኖም ግን እንቢ ያለኝስ እንደሆን? ብዬ ተጠራጠርኩ። መልሱ አሉታዊ ከሆነ የሚከተለኝን መዘዝ አሳምሬ አውቀዋለሁ። በረራውን አቋርጦ በመመለስ እጄን ለባለስልጣን እንደሚያስረክብም ጥርጥር የለውም። ስለዚህም ዝምታውን መረጥኩ።

ከቁስካኒም መንደር እንደደረስን አውሮፕላናችን ወዲያው በወታደር ተከበበች። ምናልባት በረራው አንዲት ሴት ብቻ ለማጓጓዝ የተፈፀመ መሆኑ ከከባድ ጥርጣሬ ላይ ሳይጥላቸው አልቀረም። በመሆኑም ጠመንጃቸውን እንደደገኑ ከአውሮፕላኑ ከአስወረዱኝ በኋላ ወደታማሚዋ «አክስቴ» ቤት እያጠያየቁ ወሰዱኝ።

አክስቴ እንድትሆን የተዘጋጀችው ሴትም አስቀድሞ ስለ እኔ ማንነትና አጠቃላይ ሁኔታ ቀደም ሲል በምስጢር



እንድታውቀው አድርጌ ስለነበር በወታደሮች ታጅቤ ብመጣም በፍርሃት ምትክ እንደናፈቀ ሰው ተንደርድራ ከአንገቴ ላይ ተጠመጠመች። ወታደሮቹም ይህን በመመልከት ጥርጣሬያቸው ቀንሶ ከዚያ አካባቢ እንዳልርቅ ማስጠንቀቅያ ከሰጡኝ በኋላ ወደ ጦር ሠፈራቸው ተመለሱ። ያም ሆኖ በይፋም ባይሆን በሥውር እንደሚከታተሉኝ አውቅ ነበር። ስለዚህም እስኪዘናጉልኝ ድረስ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብኝ።

በተዘዋዋሪም መንገድ ለምን ከትልቋ የአሥመራ ከተማ ለቅቄ ወደዚች መንደር ለመምጣት እንደፈለግሁ ሊያውጣጡኝ ብዙ ሙከራ አድርገዋል። እኔ ግን ምን ግዜም የማመካኘው በአክስቴ ሕመምና እንደዚሁም እራሴ በአሥመራ ውስጥ ጤና በማጣቴ ነበር።

እንደውም የልብ ልብ እንዲሰጣቸው በማለት አንዲት አነስተኛ ሱቅ ከፍቼ ሲጋራ፣ ዘይት፣ ከረሜላና የመሳሰለውን መሸጥ ጀመርኩኝ። በመቀጠልም የንግድ ፈቃድ እንዲሰጠኝ ማመልከቻ አገባሁኝ። ከዚያ በኋላማ ወታደሩ ሁሉ በጥርጣሬ ምትክ በፍቅር ያዩኝ ጀመር። እነሱም ተጨምረው የደንበኞቼ ቁጥር እየበዛ በመሄዱ ሱቁ ደመቀች ። በሆዴ ግን የምንግዜውም ፀሎቴ ከዚያ አካባቢ ሾልኪ ወደ ሱዳን የምገባበትን ዘዴ አምላኪ እንዲያመቻችልኝ ነበር።

ልመናዬም መና አልቀረም፣ ከዕለታት አንድ ቀን ከዚያን በፊት አይቼው የማላውቀው ሰው ወደ ሱቄ መጣ። ቀስ በቀስም እራሱን ካስተዋወቀኝ በኋላ ተመላልሶ እንደሚጠይቀኝ ቃል ገብቶልኝ ሄደ። ከጊዜ ወደ ጊዜ ግንኙነታችን እየጠነከረ በመሔዱ በመጨረሻ ላይ ወደ ሱዳን በምስጢር ሊያደርሰኝ እንደሚችል ገለጸልኝ። ሰውዬው መልካም ሰው ስለመሆኑ አልተጠራጠርኩም። ይሁን እንጂ በመንገድ ላይ ምን ሊያጋጥመኝ እንደሚችል በማሰብ መፍራቴ አልቀረም። እሱም ቢሆን ይሄን በመፍራት ይመስላል ወርቅና ጌጣጌጥ መያዝ እንደሌለብኝ አስጠንቅቆኛል።

ከመንደሯ በተነሣንበት ዕለት ማንም ሰው ትኩር ብሎ እንኳን ቢያየኝ እኔ መሆኔን ለመለየት አይችልም። ፀጉሬ ተቆርጦ ፊቴ በጥላሸትና በቫዝሊን ተለቅልቆ፣ እንደ አሮጊት ረጂም ቀሚስ ለብሼና ምርኩዝ ይዤ ላየኝ ጨርሶም መዲና ናት የሚል ጥርጣሬ አይጐበኘውም። በወታደሮቹም መካከል አቆራርጬ በማልፍበት ወቅት ውስጥ ውስጤ በፍርሃት ርዶ እግሬ ይተሳሠር እንጂ አንድም ዞር ብሎ የተመለከተኝ አልነበረም።

እንግዲህ እረጅሙን ጉዞ ተያይዤዋለሁ። ሲወራ እንደሰማሁት በመጓጓዣ ከሱዳን ጠረፍ ለመድረስ ሰባት ቀናት ያህል ይፈጃል። ታዲያ ለእንደእኔ ያለችው ደካማ እግረኛስ ስንት ወር ይፈጅ ይሆን?



# ምዕራፍ – 12

## በዱርና በጫካ ውስጥ

ያ የእግር ጉዟችን ብዙ መንገላታት ብዙ ጣርና መከራ የሞላበት ነበር። እባቡና የዱር አውሬው አያሳልፍም እሾህና አሜኬላው አያራምድም በዚያ ላይ ቀን ቀን በየጥሻው ሥር ተደብቀን መዋል አለብን። አንድ ወታደር ቢያየን አለቀልን ማለት ነው። በመሆኑም ከእይታ የተሰወረ አዝጋሚው የሌሊት ጉዞአችን የተንቀራሰሰና ብዙ ውጣ ውረድ የሞላበት ነበር።

በተለይም የእግር ጉዞ ለእንደኔ አይነቷ በበሽታ ለደደቀች ሴት ያለው ፍዳና መከራ በቃላት ሊገለፅ የማይችል ሲሆን አንድ ሰዓት ተራምጄ እንደ፣ ሆን ለግማሽ ሰዓት ያህል ትንፋሼ መለስ እስከሚልልኝ ማረፍ ነበረብኝ። ምላሴ በውሀ ጥም ደርቆ ተሰነጣጥቋል። እንቅፋት የጋጠውና እሾህ የጨቀጨቀው እግሬ ደም በደም ሆኗል፣ በጫማ እንዳልራመድ እንኳን እሱን መጐተቱና ሸክሙ አድካሚ በመሆኑ አውልቄ ወርውሬዋለሁ።

ምንም እንኳን ቀን ቀን ከየጥሻው ሥር ብንሸጐጥም የአየሩ ግለት ግን ጨርቅ የማያስለብስ ነበር። በዚህ ሁኔታ ለብዙ ቀናት ስናዘግም ከከረምን በኋላ በመጨረሻ ከአንዲት አነስተኛ መንደር ደረስን። እንደዕድልም ሆኖ በዚያ የሚከራይ ግመል በማግኘታችን የጨለመው ተስፋችን ለመለመ።



በመንደሯ ውስጥ ከምትገኝ አንዲት ሱቅ ታዛ ተጠግተን ለጥቂት ቀናትም ዕረፍት አደረግን። ሰውነታችን አገግሞ መንቀሳቀስ እንደቻልንም በዚያች አንዲት ግመል እኔን አስቀምጠው ጉዟችንን ቀጠልን። የአሁኑ እንቅስቃሴያችን ግን ከበፊቱ የተሻለ ከመሆኑም በላይ ወታደሮች በአካባቢው ባለመኖራቸው ሥጋታችን ስለቀነሰ በጥቂት ቀናት ውስጥ ከሱዳን ድንበር ደረስን። ለአምላክ ክብር ምስጋና ይድረሰውና ወደ ሱዳኗ የከሰላ ከተማ የሚያደርስ የአቶቡስ ቲኬት ቆርጠን እንደልባችን ተዝናንተን ለመጓዝ በቃን።



ከሰላ የተለያዩ ሕዝቦች ብሔሮችና ብሔረሰቦች የተጠራቀሙባት ከተማ እንደመሆኗ የማይሰማው የቋንቋ ዓይነት የለም። በተለይም ደግሞ አረብኛ በብዙው ሥፍራ የሚነገር በመሆኑ በየእለቱ ጥቂት ጥቂት ቃላትን ማጥናት ጀመርኩ። ምንም እንኳን ይህን ቋንቋ በመናገሬ የሱዳን ወይም የሌላ የአረብ አገር ዜጋ የመሆን ጉጉት ያደረብኝ ባይሆንም ለማወቅ ስል ግን ጠንክሬ እከታተል ነበር።

በተለይም ከአቶብስ ጣቢያው እንደወረድኩ የተዋወቅነው አንድ ጐልማሣ ከበርቴ ከነበረችው እናቱ ቤት በግርድና ስላስቀጠረኝ በነጋ በጠባው የምሰማውም ሆነ የምናገረው አረብኛ ስለነበረ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሐሳቤን ልገልጥበት ችዬ ነበር። በዚያ ቤት ውስጥ ያሳለፍኩት ሕይወት ከቀድሞው ሁኔታዬ ጋር ሲነፃፀር እጅግ የተሻለ ቢሆንም፡ በመሀሉ ግን በቤቱ አባወራ ላይ ያልታሰበ አደጋ ደርሶ በመሞቱ ያሰላምና ደስታ ሰፍኖበት የነበረው ቤተሰብ ተበጣበጠ። እኔም በመሀሉ ግራ በመጋባቴ ያንን ቤት ብቻ ሳይሆን ከተማውን ጭምር ለቅቄ ወደ ካርቱም ለመጓዝ ወሰንኩ።

አሰሪዬ ለእኔ መልካም አመለካከት እንዳላት አውቅ ስለነበረ ስለዕቅዴ አማከርኳት። እርሷም ያልከፈለችኝን ደመወዝ

በሙሉ አጠቃልላ በመስጠት እንድሄድ ተባበረችኝ ከል ጆቿም አንዱ የአቶቡስ ቲኬት ቆርጦ አሳፈረኝ።

በአጋጣሚም ቀደም ሲል ከመቀሌ ወደ ካርቱም የመጣች የአንዲት ሴት አድራሻ አግኝቼ ስለነበረ ከከተማው እንደደ ረስኩ በቀጥታ የእርሷን ቤት ማፈላለግ ነበር የጀመርኩት። ከቤ ቷም እንደደረስኩ ያደረገችልኝ አቀባበል ጥሩ ነበር። በዚያም ለአንድ ሳምንት ያህል ከቆየሁ በኋላ ስለወደፊቱ ዕድሌ ማቀድ ጀመርኩኝ።

አንድ ቀን ከተማውን እየተዘዋወርኩ ሥራ በማፈላለግ ላይ እንዳለሁ ድንገት ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ደረስኩኝ። እንደ እውነቱ እግዚአብሔርን የምናስታውሰው በችግራችን ጊዜ ብቻ ነው። እኔም ብሆን ፈጣሪዬን በተለይ የምነዘንዘው አንድ ዓይነት ፈተና ሲያጋጥመኝ ነው። በዚያን ዕለት ከዚያን ቤተ ክርስቲያን ግቢ ቆሜ እንባዬን በማፍሰስ አምላኬን ተማፀ ንኩት ለእኔ ሊሆን የሚችል ስራ ይሰጠኝ ዘንድ አፍአውጥቼ በድፍረት ጠየኩት። በዚያ ጭር ባለ ቤተክርስቲያን ውስጥ በእ ኔና በአምላኬ መካከል ሰዓታት የፈጀ ሙግትና ክርክር ተካሄደ።



በመጨረሻም ገና ከቤተክርስቲያኑ ወጥቼ ከዚያን ቀን በፊት ሄጄበት ወደማላውቀው መንገድ እንዳመራሁ ከአንድ ሕንፃ ፊት ለፊት በረድፍ የተሰለፉ ወንዶችና ሴቶች አየሁኝ። እኔም ስለነገሩ ጠጋ ብዬ ስጠይቅ መሥሪያ ቤቱ ሥራ አጦችን የሚመዘግብ ስለመሆኑ ተረዳሁ። ምንም ባለማወላወል ከሴቶቹ ረድፍ ተደባለቅኩኝ። ተራዬም ደርሶ ከመዝጋቢው ዘንድ እንደቀረብኩኝ በቅድሚያ ደጋግሞ ካየኝ በኋላ ስሜን ጠየቀኝ። እኔም «መዲና» ብዬ ገና ከመናገሬ እራሱን በአዎ ንታ ነቀነቀና ከሱዳን ውጪ ለመቀጠር ስለመፈለግ አለመፈለጌ ጠየቀኝ። ይህ ያልታሰበ ዜና የልቤን ትርታ ቢጨምረውም እየተቻኮልኩ ፈቃደኛ ስለመሆኔ ገለጽኩለት።

የሚገርመው ነገር ይህ ሰው ስለመታወቂያ ወረቀቴ እንኳን አልጠየቀኝም ነበር። ምናልባትም ከስሜ ሙስሊም ትሆናለች ብሎ ስለገመተም ሊሆን ይችላል። ብቻ አንድ ያልተጠበቀ የምሥራች አበሠረኝ። ይኸውም ወደ ሳውዲ አረቢያ በመሄድ በንጉሡ ቤተሰብ ውስጥ በቤት ሰራተኛነት ለመቀጠር መቻሌን የሚገልጽ ነበር። እርግጥ ሙስሊም አለመሆኔ ብዙ ችግር እንደሚያስከትልብኝ ባውቅም እኔ ግን

አምላኬ ከጐኔ እስካለና የእርሱም ፈቃድ እስከሆነ አንዳችም ችግር እንደማያጋጥመኝ በመተማመን ስምምነቴን አስታ ወቅኩት።

ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና በተመዘገብኩ በሳምንቱ ወደ ሳውዲ አረቢያ በሚያደርሰኝ አውሮፕላን ተዝና ንቼ በመብረር ላይ ነበርኩ።



# ምዕራፍ 13

## ከግርድና ወደ ልዕልትና

እግሬ ከንጉሡ ቤተ መንግሥት በረገጠ ጊዜ የማየውን ነገር ሁሉ ጨርሶም ለማመን አልተቻለኝም፤ የሕንፃው ውበት የየክፍሎቹ ማማርና ማሸብረቅ የቤት ዕቃዎቹ ጥራትና ውበት የሕልም ዓለም እንጂ በእውን ያለ አይመስልም። የጠበቀኝ ምቾት ከገመትኩት በላይ ነበር። ያስፈለገኝን ምግብና መጠጥ የማማረጥ፣ በግል መኝታ ክፍሌ ውስጥ እንዳሰኘኝ የመዝናናት ሙሉ መብት ነበረኝ። የእኔ የሥራ ድርሻ ከንጉሡ ልጆች አንዲቷ የሆነችውን ልዕልት መንከባከብና የምታዘኝን መፈፀም ብቻ ነበር።

እንግዲህ ኑሮዬ ይህን ይምሰል እንጂ አንድ ያልጠበቅኩት ነገር በመሀሉ ተከሰተ። አንድ ዕለት ልዕልቲቱን እጅግ ቀርቤ እያለባበስኳት እንዳለሁ ለካስ ወደ እጄ አየት አድርጋ ኖሯል። ወዲያውኑም ሰውነቷ በቁጣ ተለዋወጠ፤ ከአጠገቧ ገፍትራም አራቀችኝ ። ለጊዜው ፍጹም ግራ ተጋባሁ። ሆኖም እኔም ዓይ ኖቼን ወደ እጄ ወርውሬ ስመለከት ምክንያቱን አወቅኩት። ነና በሕፃንነት ዕድሜዬ እናቴ ከእጄ ላይ የመስቀል ቅርፅ ነቅ ሳኝ ነበረ እንደፈራሁትም ልዕልቷ «አንቺ ደፋር እንዴት

ክርስቲያን መሆንሽን ሳትነግሪኝ።» ስትል ጮኸችብን። እኔ ግን ለጊዜው ብደናገጥም ክርስቲያንነቴን የምክደው አል ነበረም። በእርሷ ግምት ሥራ ለማግኘት ስል ስምና ሃይማኖቴን የቀየርኩ መስሏታል። እኔ ግን ይህንን ሁሉ አለማድረጌን ስገለጽላት ድፍረቴም ጭምር እንደሆነ እንጇ ለጠለጠ ንዴት ጋበዛት።

ከዚያን ዕለት ወዲህ በዚያ ግቢ ውስጥ እንደ ፀያፍ ነገርና እንደባይተዋር እታይ ጀመር። ለወትሮው ይቀርቡኝ ከነበሩት አንዳንዶቹ ግን ሃይማኖቴን ቀይሬ ሙስሊም እንድሆን እንደአቅማቸው ሳይመክሩኝ አልቀረም። እንዳውም እስልምናን በመቀበል በአጭር ጊዜ ውስጥ ከበርቴ ልሆን እንደምችል ጭምር በመግለጽ ሊያግባቡኝ ሞክረው ነበር። እኔ ግን በቀላሉ አልተረታሁላቸውም። በመጨረሻም ክርስቲያኖች ዋሾዎችና ሰካራሞች በመሆናቸው በሰማይ የሚጠብቃቸው የሲዖል ሥቃይ መሆኑን በማብራራት በቀላሉ እስልምናን ተቀብዬ ወደ ገነት ለመግባት እንድችል ሊያሳምኑኝ ከፍራተኛ ጥረት አደረጉ። እኔ ግን ልፋታቸውን ሁሉ አከሸፍኩት።

በዚህ መሀል ልዕልቲቱ በቅርቡ የአጐቷን ልጅ ለማግባት በሽር ጉድ ላይ እንደመሆኗ፣ ለሠርጓ የሚያስፈልጓትን ጌጣጌጦች ለመግዛት ባህር አቋርጣ ወደ አውሮፓ ለመሄድ



በመዘጋጀት ላይ ነበረች። ታዲያ በሃይማኖቴ የተነሣ የቱንም ያህል ልታርቀኝ ትሞክር እንጂ፣ ለአውሮፓው ጉዞ ግን እንደማስፈልጋት አምናበታለች። በሱዳን ቆይታዬ ወቅት በመጠኑም ቢሆን እንግሊዝኛ መናገር ሞካክሬ ስለነበረ በአስተርጓሚነት እንደማገለግላት ብሎም በክርስቲያንነቴ ተጨማሪ ድጋፍ እንደማበረክትላት ሳትረዳው አልቀረም። ከሳውዲ አረብያም መናገሻ ከተማ ከሪያድ በመነሣት በቀጥታ የበረርነው ወደ ለንደን ነበር። ለልዕልቲቱ ማረፊያ እንዲሆን የተመረጠላት ቤት ከንግሥት ኤልሳቤጥ ቤተ መንግሥት እምብዛም አይርቅም። ከዚያን ዕለት ጀምሮ ከልዕልቲቱ ጐን ጨርሶም መለየት አልተፈቀደልኝም። በምንሄድበት ቦታ ሁሉ ሌሎች የሚናገሩትን በማዳመጥ እንደነገሩ የምተረጉምላት የእርሷንም መልስ አዳምጬ የማስረዳላት እኔ ነበርኩኝ።

ለንደን በቆየንባቸው ቀናት ሁሉ፣ መኪናዎችን እንደ ልብስ በመቀያየር እጅግ የተቀናጣ ሕይወት ብንመራም ከልዕልቲቱ አጠገብ የምንደርሰው እኔና ምናልባት እንግሊዛዊው ሹፌሯ ብቻ ነበር ለማለት ይቻላል።

ከአንድ ወር የለንደን ቆይታ በኋላ ወደ ፓሪስ በረርን። እዛም እንደደረስን አንዳንድ ፎቶ ግራፎች የማንሣት ጉጉት ስላደረብኝ ሹፌሩን ካሜራ እንዲገዛልኝ አደረግኩኝ። እንደ እውነቱ በፓሪስ ያሳለ ፍነው ጊዜ እስከመቼም ከኅሊናዬ



የማይፋቅ የደ ስታወቅት ነበር። በውኔ ቀርቶ በሕልሜም አስቤ የማላውቀውን ምቾትና ድሎትን ተለማመድኩት። ንጉሥ ሰሎሞን፡ «በነገሥታት መኖሪያ ግቢ ውስጥ አይጦችም ጭምር ይፈነጩበታል» ያለውን አስታወስኩ። እኔም ከሁሉም ተንቄ የነበርኩት ምስኪኗ መዲና አሁን ከንጉሥ ልጅ እኩል ተንቀባርሬ የመኖር ዕድል አጋጥሞኛል። ክብሯ እንዳይቀነስ በመሥጋት፣ ምርጥ ምርጥ ልብሶችና ጌጣጌጦች ጭምር ይገዛልኛል። ለእርሷ የሚዘጋጀውን ምግብ እኩል እመገባለሁ፣ ከርሷ ባሉመለየቴም በምታማርጣቸው ሽንጣምና ዘመናዊ መኪኖች እንሸራሽ ራለሁ። ኑሮ ይሏል ይቺ ናት! ስለእውነት የዚያን ጊዜውን ሕይወቴን በካሜራ ባልቀርፀው ኑሮ እኔም



ብሆን በገሃዱ ዓለም ያለፍኩበት ስለመሆኑ መጠራጠሬ ባልቀረም።

ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ተድላና ደስታ አላፊ ነው። ልዕልቲቱ በዚህ በአውሮፓ ሽርሽራችን ሳቢያ በመጠኑም ቢሆን ልታቀርበኝ ሞክራለች። ሆኖም ግን ወደ ሳውዲ አረቢያ ከተመለስን በኋላ ይህ ፀባዩዋ ይቀየር ይሆን? እኔ እንጃ!... ይሄንን እግዚአብሔር ብቻ ያውቃል።

እግዚአብሔር በለገሠኝ በዚህ ያልተጠበቀ ችሮታ መደሰቴን ገፋሁበት። ከፓሪስ ቀጥሎ የበረርነው ወደ ኢጣሊያዋ ከተማ ቬኑስ ነበር። ይህች ከተማ ከውብም ውብ እንደመሆኗ ተዟዙሬ ልጠግባት አልቻልኩም። እንደውም አንድ ቀን ይሉኝታ ቢስነት አጥቅቶኝ ከልእልቲቱ ፊት ፎቶግራፍ ለመነሣት በመድፈሬ ያንን ካሜራ እስከመነጠቅ ደርሻለሁ። በዚህ መልኩ ስድስት ወራት ያህል ካሳለፍን በኋላ ወደ ሳውዲ አረቢያ የመመለሻችን ዕለት ተቃረበ። አንድ ምሽት እኔና ልዕልቷ በአሥረኛው ፎቅ ላይ ከሚገኘው አፓርትማችን ውስጥ ተቀምጠን እንዳለን አንድ ያልጠበቅኩት ጥያቄ አቀረበችልኝ። ይኸውም ሙስሊም ለመሆን ፈቃደኛ መሆን አለመሆኔን የተመለከተ ነበር። እኔም በዚህ ባልታሰበ ጥያቄዋ ከመገረምም አልፌ በመደነቅ፣ «ለምን ትቀልጃለሽ! እኔ ሃይማኖቴን በምንም ነገር አልለውጠውም» ስል መለስኩላት።

እርግጥ ነው አመላለሴ ቅፀበታዊ ስለነበረ የጓደኛ ያህል ተዳፍሬያት ነበር ለማለት እችላለሁ። በዚህም የተነሣ ነው ከተቀመጠችበት ተወርውራ በጥፊ ያጮለችኝ። ከዚያም

ከወለሉ ላይ ጥላ በርግጫ በጡጫ ትደበድበኝ ጀመር። በበኩሌ እርዳታ እንዲደርስልኝ ከመጮህ በስተቀር እራሴን ለመከላከል አልሞከርኩም። በመጨረሻም ላይ መዳከሜን አይታ በመስኮት ልትጥለኝ በመጎተት ላይ እንዳለን ፓሊሶች በሩን እንኳኩተው ገቡ። ምናልባት የሕግ አስከባሪዎቹን የጠሯቸው ጩኸቴን የሰሙ ከእኛ አፓርትማ ጐን ያሉ ሌሎች ተከራዮች ሳይሆኑ አይቀሩም ብዬ አሰባለሁ።

የመጡት ፓሊሶች አዛዥ አረብኛ መናገር ባለመቻሉ ለእኔ አንዳንድ ጥያቄዎችን በእንግሊዝኛ ያቀርብልኝ ጀመር። ልዕልቲቱ ይህን በመመልከት ስለፈፀመችብኝ ግፍ እንዳ ልናገር አስጠነቀቀችኝ። እኔ ግን ለጥላችን መንስዔ ከሆነው መክንያት አንስቼ በዝርዝር አስረዳሁ። ይሁን እንጂ በሰላሙ ጊዜ ያደረገችልኝን መልካም ነገር በማሰብ ልዕልቲቱን ወደ ፓሊስ ጣቢያ እንዳይወስዱና እንዳያጉላሏት ልከሳት አለመፈለጌን ገለጽሁ። ፓሊሶቹም የነገሩን አዝማሚያ በመረዳት ምናልባትም ወደ ትውልድ አገሬ የመመለስ ፍላጐት ካለኝ ሊተባበሩኝ እንደሚችሉና በማግሥቱም ከጣቢያ ድረስ በመሄድ ስለውሳኔዬ እንዳሳውቃቸው ገልፀውልኝ ተለያየን።



# ምዕራፍ – 14

## የነፃነት ዋዜማ

ወደ ካርቱም በመመለሴ በአንድ በኩል ልደሰት እንጂ ተመልሼ ለድንቁርናና ባርነት መዳረጌ እየታወሰኝ ማዘኔ አልቀረም። ልዕልቲቱ ያን ግፍ በፈፀመችብኝ በሳምንቱ በፍራንክፈርት በኩል አድርጌ ወደ ሱዳን በመብረር ላይ ነበርኩኝ። የዓባይ ወንዝ በክረምቱ ወራት በጐርፍ እንደሚጥለቀለቅ ሁሉ እኔንም እንደዛው የከበደ ጭንቀት ነበር የወረረኝ። ዕድሜዬ አሁንም በአሥራዎቹ ውስጥ ቢሆንም፣ ብዙ መራራ ገጠመኝና ልምድ በማሳለፌ እንደቀድሞው በየቡና ቤቱ በአሻሻጭነት ለመቀጠር ሐሳቡም ምኞቱም አልነበረኝም። ደግሞም እኮ ወደ ሳውዲ አረቢያ ከሄድኩበት ጊዜ ጀምሮ የችግርን ሕይወት ረስቼው ነበረ። ለስሙ ልዕልትነቱ ቀረብኝ እንጂ አኗኗሬ ለእኔ ከልዕልታቱ ያነሰ አልነበረም።

በሱዳን ውስጥ ለዳግመኛ ባሳለፍኳቸው ጊዜያት እራሴን የመመርመርና የመመዘን ዕድል አጋጥሞኝ ነበር። እንደ መደበኛ ተማሪዎች በቂ የጽሕፈት ችሎታ ባይኖረኝም ጥቂት የውጭ ቋንቋዎች በመጠኑም ቢሆን የመናገር ችሎታ አዳብሬ ነበር። ለዚህ ሁሉ ያበቃኝ ቸሩ ፈጣሪዬ መሆኑን በማወቅ

እርሱን ከማመስገን የተቆጠብኩበት ወቅት የለም። ትዳር ለመያዝ ስለሚናረኝም ዕድል በአእምሮዬ ማብሰልሰሌ አል ቀረም። በዚያ በጨቅላ ዕድሜዬ ውስጥ በየቡና ቤቱ በመቀጠር ለአያሌ ወንዶች መደሰቻና ስሜት ማርኪያ ሆኛለሁ። ከዚያ በተረፈ ግን በእውነተኛ ፍቅር ተነሳስቶ የትዳር ጓደኛው ሊያ ደርገኝ የጠየቀኝ ሰው የለም። ሆኖም ስለወደፊቱ ዕድሌ እያሰ ብኩ የዕድሜ ልክ የብቸኝነት ሕይወት ያጋጥመኝ ይሆን? በማ ለት መጨነቄ አልቀረም። እርግጥ ይህንንም ቢሆን ለእግ ዚአብሔር ትቼው ነበር።

በካርቱም ቆይታዬ የምኖረው ከትግራይ ከመጡ ቤተሰ ቦች ጋር ተዳብዬ ነበር ። በእጄ ላይ መጠነኛ ገንዘብ በመኖሩም ለጊዜው ሥራ ለመያዝ አልተቻኮልኩም።— ታዲያ አንድ ቀን ከቤቱ አባወራ ጋር በመወያየት ላይ እንዳለን ስለወደፊቱ ዕቅዴ አንስቶ ጠየቀኝ። እኔም አንድና ብቸኛው ምርጫዬ ወደ ጀር መን ለመሄድ መሆኑን ነገርኩት። በዚህ ሳቢያ ነበር እርሱ ከሚ ያውቀው ከአንድ የተጭበረበረ ፓስፖርትና ቪዛ አዘጋጅ ግለሰብ ጋር ለመተዋወቅ የበቃሁት።

ሰውዬው ለዚህ ተግባር ማሳኪያ ስድስት ሺህ ዶላር እን ድከፍለው ከመጠየቁም ሌላ ከሱዳን ለመውጣት የምችለው በስደተኛ ስም እንደሚሆን አስታውቆኝ ነበር። በዚህም



ከተስማማን በኋላ ገንዘቡን አዘጋጅቼ ከአንድ ቦታ እንድንገናኝ ቀጠሮ ሰጠኝ። በቀጠሮውም ዕለት ተገናኝተን መኪናው ውስጥ ካስገባኝ በኋላ ጭር ወደአለ አካባቢ ወሰደኝ። በዚያም ሥፍራ ገንዘቡን እንዳስረክበው ጠየቀኝ። እኔም በእጄ ላይ ያለው ብር የተጠየኩትን ያህል ስላልሞላልኝ ጌጣጌጦቼን ሁሉ አሰባስቤ ሰጠሁት። ከሦስት ቀናት በኋላ ፓስፖርቱንና ቪዛውን ከእጄ እንደሚያስገባልኝ የተስፋ ቃል ሰጥቶኝ ተለያየን። ፍጹም ቂልነቴና ጅልነቴ የታወቀኝ ግን የኋላ ኋላ ነበር።

ሦስቱ ቀናት እንደ ዋዛ አለፉ። የእኔም ውሎዬ ከአሁን አሁን ይመጣል በማለት ከቀጠረኝ ቦታ ተገትሬ መዋል ሆነ። ሰውዬው ግን የለየለት አጭበርባሪ ኖሯል። ገንዘቡንም ሳስ ረክበው ጭር ወዳለ ቦታ የወሰደኝ ያለ ምክንያት አልነበረም። ከሰው እይታ በማራቅ ምስክር ለማሳጣት ነበር። ቀናት አል ፈው ሳምንታት እየተተኩ ሄዱ። ይህን ጊዜ ነበር ተስፋ በመ ቁረጥ ለጊዜው እንኳን መተዳደሪያ የሚሆነኝ ሥራ ማፈላለግ የጀመርኩት። የዕድል ነገር ሆኖም እነዚያ ያስጠጉኝ ሰዎች በአንዳንድ የቤት ውስጥ ሥራ እየረዳኋቸው እንድቀመጥ ስለ ፈቀዱልኝ ጭንቀቴ በመጠኑም ቢሆን ተቀርፎ ነበር።

ለችግር ቀን ይሆነኛል ብዬ ያሰብኩትና ደክሜ ያገኘሁትን ገንዘብና ጌጣጌጤን አጭበርብሮ የወሰደብኝ ያ ኤርትራዊ ሰው

ያን መሰሉን በደል ቢፈጽምብኝም እግዚአብሔር ግን በእነዚህ
ከትግራይ በመጡ ሰዎች እንድካስ ሁኔታዎችን አመቻችቶልኝ
ኖርዋል።

ያም ሰው ከካርቱም ጠፋ እኔም ለአንድ ዓመት ያህል
የጥገኝነት ሕይወቴን ገፋሁት በመጨረሻም የአሜሪካና የካናዳ
መንግሥታት የፖለቲካ ስደተኞችን እንደሚቀበሉ የሚያበ
ሥር ዜና ሰማሁ።

ከዚያን ዕለት ጀምሮ ወደ አሜሪካ ኤምባሲ መመላለሱን
ተያያዝኩት፣ ረጂሙን ጊዜዬን የማሳልፈው ከግቢው በር ተለ
ጥፌ ነው። እርግጥ ጥገኝነት የሚጠይቁት ሰዎች ቁጥር እጅግ
ከፍያለ በመሆኑ ያን ሁሉ ሕዝብ ለማስተናገድ ወራት ቢፈጅም
አያስደንቅም። እኔ ግን የሁኔታዎችን አዝማሚያ በቅርብ በማ
ጤን ዕድሉ በዓመትም ውስጥ እንደማይደርሰኝ እርግጠኛ እን
ደሆንኩኝ በአንድ ዘዴ ለመጠቀም ወሰንኩ። ይኸውም ሠራ
ተኞቹ ለሥራ ወደቢሮ በሚገቡበት ሰዓት ድምፄን ከፍ አድርጌ
በማልቀስና በማንባት ትኩረታቸውን ለመሳብና ሆዳቸውን
ለማባባት ነበር። እንደተአምርም ያ ዕቅዴ ሠራና ወዲያውኑ
ስሜ ተመዘገበ። ለአምላክ ክብር ምስጋና ይግባውና በሳምንት
ጊዜ ውስጥ ለቃለ መጠይቅ ተጠራሁኝ። አጣሪው ቡድን



ሦስት አባላት ያሉት ሲሆን ለእኔም ካቀረቡልኝ የተለያዩ ጥያ
ቄዎች መካከል አንዱና የመጨረሻው ወደ አሜሪካ ብሄድ
በምን ዓይነት ሥራ መተዳደር እንደምችል እንድገልጽ ነበረ።
እኔም እራሴን እጅግ ዝቅ በማድረግ ለማንኛውም ቤተሰብ በግ
ርድና ተቀጥሬ ለማገልገል ዝግጁ ስለመሆኔ አስረዳሁ። ከቃለ
መጠይቁ በኋላ ውጤቱን ለማወቅ ሦስት ወራት ያህል መጠ
በቅ ነበረብኝ። ታዲያ ከዕለታት አንድ ቀን እንደልማዴ የቀድ
ሞው ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ካሠሩት ቤተ ክርስቲያን
ሄጄ በመጸለይ ላይ እያለሁ። ወደ አሜሪካ ለመሄድ ካመለ
ከትነው ሴቶች አንዷ እየሮጠች ወደ እኔ መጣች። ከዚያም
ለመሄድ የተፈቀደላቸው ሰዎች ስም ዝርዝር በማስታወቂያ
ሰሌዳ ላይ መለጠፉን ከነገረችኝ በኋላ የእኔ ስም ግን ስለአ
ለመውጣቱ በጣም እየፈራች ነገረችኝ።

እኔም ለጊዜው ምርር ብዬ አለቀስኩኝ። አምላኬንም
ለምን እረሳኸኝ ስል ወቀስኩት። ሆኖም ግን በዚያን አጋጣሚ
እጅግ ታላቅ ስሕተት ፈጽሜ ኖሯል። እግዚአብሔር ለእኔ
መልካም መስሎ የታየውን ነገር ከማድረግ አንድም ቀን
ወደኋላ ብሎ አያውቅም። እኔ ግን የእሱን አሰራር ማወቅና
የስራ ጊዜውንም መጠባበቅ አልሆነልኝም። እንደምንም እራ
ሴን አረጋግቼ ጉዞዬን ወደ ኤምባሲው አቅጣጫ አደረግሁ

የዚያን ጊዜ የእኔ ወደ ኤምባሲው መሄድ እንዲያው በደመ ነፍሴ የተፈፀመ እንጂ አስቤበት ያደረግኩት አልነበረም። ታዲያ ማስታወቂያ ከሚለጠፉበት ሰሌዳ ሥር ቆሜ የተለጠፉትን የተለያዩ ወረቀቶች ስመለከት በድንገት ዓይኖቼ ለብቻው ከተለጠፈው ማስታወቂያ ላይ አረፈ። በዚያ ወረቀት ላይ የሠፈረው የእኔ ስም ብቻ ሲሆን ወደ አሜሪካ የመሄድ ዕድል በመጨረሻ ላይ እንደተሰጠኝ የሚያበስር ነበር።

ያ በውስጤ ሰላም ነስቶኝ ሁሌም በምኞት ያስጋለበኝ የነበረው ቀን ደረሰ ከእንግዲህ የቀረኝ ከአሜሪካ ኅብረተሰብ ጋር እንዴት መኖር እንደምችል የሚያስተዋውቀውን የልምድ ፕሮግራም መከታተል ብቻ ነው። በመጠኑም ቢሆን ስለ አሜ ሪካ ታሪክና ባህል መሠረታዊ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል። እንደ ዚሁም ከሕዝቡ ጋር እንዴት ለመግባባት እንደምንችል የሚረዳን የንግግር መርሐ ግብር ተመድቦልንም ነበር።

በተጨማሪም በአሜሪካ ውስጥ በምንኖርበት ወቅት ችግር ቢያጋጥመን ሊረዱን ፈቃደኛ ስለሆኑት ቤተሰቦች ማንነትና አድራሻ ገለፃ ሲደረግልን ቆየ። ለእኔ ኃላፊነቱን የወሰድት በባ ልቲሞር ከተማ የሚገኙ ባልና ሚስቶች ነበሩ። ዛሬም ከልጅነቴ ጀምሮ ለሚገጥሙኝ ፈተናዎች ሁሉ እንዲታደገኝ ወደማለቅስበት በደስታ እንባ የታጀበ ድምፄን አሰማሁ።



ሁሌም «አይዞሽ» ሲለኝ እስከመቼ? ወደምለው ጌታዬ ቀና አልኩኝ።

እሱም «ዘንበል አለልኝ»።

አሁን ከሱዳን ምድር የምለቅበት ጊዜ እየተቃረበ መጣ። የሚገርመው ነገር ደሞ ለወትሮው በደንብ የማላውቃቸው ሰዎች እንኳን ሳይቀሩ አሁን አገር ለቅቄ ለመሄድ በዝግጅት ላይ መሆኔን ሲሰሙ እንደየአቅማቸው የገንዘብ እርዳታ አደረጉልኝ። ስለእውነት ከሆነ ወርቅ ጭምር ሳይቀር የለገሱኝ ሰዎችም ነበሩ። የእነኝህን ሁሉ ግለሰቦች ልብ ያራራልኝ እግዚአብሔር ቢሆንም እነሱ ለኔ ለአንዲት ከርታታ ሴት ያላቸውን ፍቅርና አለኝታነታቸውን ስለገለጹልኝ ለእያንዳ ንዳቸው ፍቅርና ባለውለታነት እኔም በጊዜው ያለኝን እንባ ዬን ብቻ እያፈሰስኩ ገልጬላቸዋለሁ።

– ሌላማ ምን ላደርግላቸው እችላለሁ?

እነሆ! እኔን ምስኪኒቱን እግዚአብሔር ከትቢያ ላይ አን ስቶ ወግ ማዕረግ አግኝበታለሁ ብዬ ወደ ማስብበት አቅጣጫ እየመራኝ ነው። ለዚህም ሱዳንን ለቅቄ ወደ አሜሪካ በሚወ ስደው አውሮፕላን ላይ እንደ እኔ ዕድለኛ ከሆነች ሌላ ሴት ጋር ጐን ለጐን ተቀምጠናል.

ለአምላክ ታላቅ ክብርና ምስጋና ይድረሰው!

## ክፍል – 3

# ምዕራፍ 15

## የባህል እንግዳ

ወደ አሜሪካ በምናደርገው ጉዞ ጣልቃ ለአንድ ሳምንት ያህል የግሪክ መናገሻ ከተማ በሆነችው በአቴንስ እንድንቆይ ተደረገ። በዚህ ዕድል በመጠቀም ያቺን ታሪካዊ ከተማ ከዳር ዳር ለማዳረስ ችያለሁ። እንደውም ከተማዋን በምንለቅበት ወቅት ከአውሮፕላን ማረፊያው የደረስኩት እጅግ ዘግይቼ ነበር። በዚህ በረራችን ላይ አንድ ያልታሰበም ነገር አጋጥሞኛል። ይኸውም ሁለት ሴት አሜሪካዊያን የግድ ፎቶግራፍ ካላነሣንሽ በማለት አጥበቀው ጠየቁኝ። እኔም እጅግ በመደነቅ ለምን? ስለ ጠየቅኳቸው። የሰጡኝ መልስ ደግሞ ጨርሶም ያልጠበቅኩት ነበር። ለካስ እነሱ በውበቴ ከግብጿ ንግሥት ክሌዎፓትራ በቅርቤ ከአሜሪካዊቷ ተዋናይ ዲያና ሮዝ በጠይምነቴ ከደቡብ አፍሪካዊቷ አቀንቃኝ ማሪያ ማኬባ ጋር አወዳድረውኝ ነበር። እኔም በዚህ ባልተጠበቀ መሞካሸት ደስታም ኩራትም ተሰምቶኝ ምንስ ቢሆን የንግሥት ሳባ ዘር አይደለሁ! ስል ውስጥ ውስጡን ትምክህት ብጤ አደረብኝ። ከአሁኑ አድናቆትን ካተረፍሁ አሜሪካ ስገባ ተመሳሳይ ትኩረት ስለመሳቤ



ውስጥ ውስጤን እንደ መኩራራት ከጀለኝ ለካስ ቆንጆዩ ኢትዮጵያዊ ኖሬአለሁ ብዬም አሰብኩ።

አውሮፕላናችን በሚያዝያ ወር 1984 ዓ.ም. በኒውዮርክ ከተማ በሚገኘው የጆን ፊትዝጀራልድ ኬኔዲ አውሮፕላን ማረፊያ አኰብኩቦ ቆመ። ከጥቂት ቆይታም በኋላ በአሜሪካ እንደቤተሰብ ሆነው ሊያስጠጉኝ ፈቃደኛ የሆኑት ቤተሰቦች ወደሚገኙበት ወደ ባለቲሞር ከተማ ጉዞዬን ቀጠልሁ። ከዚያም እንደደረስኩ ያደረጉልኝ አቀባበል እጅግ ሞቅ ያለ ነበር። በተለይም እንግሊዝኛ በመናገሬ መገረማቸውን ሳይደብቁ ገልጸውልኛል። በተመሳሳይ ሁኔታ በአለባበሴም ሆነ በጌጣ ጌጦቼ የማሳፍር አልነበርኩም»

ስለ እውነት ለመናገር እኔው እራሴ ከበርቴ ጥቁር አሜሪካዊት እንጂ ከቶም በጥገኝነት የመጣሁ ኢትዮጵያዊ አልመስልም ነበር። በሁኔታዬም በመሳባቸው ይመስለኛል ብዙዎቹ ገልመጥ ብለው በአድናቆት ሳያዩኝ አያልፉም። በዚያን ጊዜ ሁሉ በሆዴ ለአምላኬ ምስጋና እያቀረብኩኝ ነበር።

እነሆ ልመናዬን ሰምቶ ለነፃይቱ አሜሪካ ምድር አብቅቶኛል። ከባልቲሞሩ ያልጠበቅኩት ደመቅ ያለ አቀባበል በኋላ ለጊዜው ማረፊያ እንዲሆነን ወደ ተዘጋጀልን የወጣት ሴቶች ክርስቲያናዊ ማኅበር ሕንፃ ተወሰድን። በግቢው ውስጥ

እንደኛው ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የመጡ አያሌ ሴቶች ነበሩ። እንደ እውነቱ ያንን ግቢ የባህል ማዕከል ነበር ለማለት ይቻላል። የቋንቋው የአለባበሱ፣ የአመጋገብና የንግግሩ መቀያየጥ እንደ እኔ ላለው እንግዳ ለጊዜውም ቢሆን ማስደንገጡና ግር ማለቱ አይቀርም።

ከሕንፃም ውጪ የሚያጋጥሙን ብዙ ችግረኞች ሰዎች ነበሩ። እኔም በእጄ ላይ ካለው ገንዘብ እንደአቅሜ መመፅወቴን አላቋረጥኩም። ውሎ ሲያድር ግን ከገንዘቤም መመንመን ሌላ ብቸኝነት እያጠቃኝ በመሄዱ ሥራ ማፈላለግ ጀመርኩኝ። ከዚያም ወደ ሂያት የሠራተኞች ቅጥር መሥሪያ ቤት በመሄድ አዲስ ተቀጣሪዎች ማሟላት የሚገባቸውን ፎርማሊቲ አጠናቀቅኩኝ።

ወር ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ሥራ ባገኝም አሁንም ችግሬ የመኖሪያ ቤቴን ለመቀየር ካለመቻሌ ላይ ነበር። ታዲያ አንድ ምሽት የቴሌቪዥን ፕሮግራም በመከታተል ላይ እንዳለሁ ሰባኪው ፖት ሮበርትሰን እንደ እኔ ዓይነት ችግር ስላጋጠማቸው ሰዎች አንሥቶ በእግዚአብሔር መታመን እንደሚገባቸው አጠንክሮ ካሳሰበ በኋላ አንድ ያልተጠበቀ መልእክት አስተላለፈ። ይኸውም ከዘመድ ወገኖቿ ተለይታ መኖሪያ ቤት በማጣት የምትጨነቀው ሴት ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ



ተቀባይነት አግኝቶ ምኞቷ ሁሉ በቅርቡ እንደሚሟላላት የሚያበሥር ነበር። በዚያን ጊዜ መልእክቱ በቀጥታ ለእኔ የተላለፈ ያህል ተሰምቶኝ ከመቀመጫዬ በመነሣት የደስታ እንባ አፈሰስኩ።

የሚገርመው በዚያኑ ሳምንት ውስጥ የተሻለ ሥራ ማግኘት ብቻ ሳይሆን አንድ ራሱን የቻለ ክፍል ያለው አፓርትማም ለመከራየት ቻልኩኝ። ከዚያም ውጥንቅጡ ከወጣ ሕንፃ ወጥቼ የሰላም ሕይወት መምራት ጀመርኩኝ። አጐራባቾቼም መልካም ሰዎች በመሆናቸው በእጅጉ ይቀረቀሩልኝና አካባቢውንም እንድለማመደው ያበረታቱኝ ነበር። በተለይም ከእኔ ክፍል ቀጥሎ ባለው ክፍል የምትኖረው ልጃገረድ በጣም ትቀርበኛለች። እርሷም የኰሌጅ ተማሪ እንደመሆኗ ለማጥናት ስትል እኩለ ሌሊት እስኪያልፍ ድረስ ታመሽ ነበር። በመሆኑም በአንዳችን ላይ እንኳን የሆነ ችግር ቢፈጠር በመሀላችን ያለውን ግርግዳ በመምታት በምልክት ‹ድረሺልኝ› ስንል መልእክት ለመለዋወጥ ተስማምተን ነበር።

እኔም ብሆን ውዬ ባደርኩ መጠን መንፈሴ እየተረጋጋ፣ ልቦናዬም እየተበራታ በመሄዱ ወደ አፓርትማዬ እያመሸሁ መመለሱን ተለማመድኩት። እንዲያውም ሌላ ቀርቶ ጌጣ ጌጦቼን ለማድረግ እንኳ ድፍረት ሊሰማኝ ጀምሮ ነበር።

ለካስ በዚህ መሀል አንድ የከተማ ወንበዴ የእንቅስቃሴዩን ሁኔታ ሲያጠና ቆይቶ አንድ ምሽት ሲከታተለኝ ኖሯል። እኔም በደመ ነፍሴ በጨለማው ውስጥ አድብቶ የሚጠብቀኝ ሰው እንዳለ ተሰምቶኝ ሮጬ ወደ አፓርትማው ሕንፃ በመ ግባት ወደ ክፍሌ በማምራት ላይ እንዳለሁ አንድ ጠንካራ እጅ ከየት መጣ ሳልል ከኋላ አፈነኝ። በቀጥታ ወደ ክፍሌ እን ድገባም ከኋላዬ በጉሽም ይደስቀኝ ጀመር። ጓደኛዬ እን ድታስጥለኝ በማሰብ ከእሷ ክፍል አጠገብ እንደደረስኩ ቀደም ሲል እንደተመካከርነው ግርግዳውን መታ፣ መታ አደ ረግኩት። እሷም ወዲያውኑ በሯን ከፍታ ስትወጣ ዓይቶ ኖሮ እኔን በአንድ እጁ ይዞ በሌላው እጁ ሽጉጡን ደገነባት። ከዚያም እየጐተተኝ ወደ እርሷ ክፍል ውስጥ አስገባኝ። ለካስ በዚያ ክፍል ውስጥ ቀደም ሲል የመጡ የእርሷም የትምህርት ቤት ጓደኞች ኖረዋል።

ሰውዬው ሁላችንንም በሽጉጡ በማስፈራራት ከአንድ ግር ግዳ ጥግ ካስቆመን በኋላ ጌጣጌጣችንን አንድ በአንድ ማስወለቅ ጀመረ። በዚያን ወቅት የእኔ ሥጋት በመጨረሻ ላይ ይገ ድለናል የሚል ነበር። ሐብልና ጉትቻችንን፣ አምባርና ቀለበታችንን በሙሉ ካስወለቀና በየኪሶቹ ካጨቀ በኋላ የተ ቀሩትን በሙሉ እርስ በርስ በማቆራኘት አሠራቸው። እኔን ግን በጭካኔ ወርውሮ ከምንጣፉ ላይ ካጋደመኝ በኋላ ቀሚሴን



ወደላይ በመሰብሰብ ሙታንታዬን ከጭኖቼ መሀል ተረተረው። ወዲያውኑም ሱሪውን ተቻኩሎ በመፍታት ያለ እንዳች ይሉኝታና ኀፍረት የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጸመብኝ። ይህን መሳዩን አሳፋሪና አስነዋሪ ግፍ እንዳይፈጽምብኝ እን ባዬን በማፍሰስ ብለምነውም እርሱ ግን በአጸፋው በጭካኔ በሽ ጉጡ አፈሙዝ ከአገጬ ላይ ስለመታኝ ከዚያን ወዲያ ዝም ብዬ የሚደርስብኝን ሁሉ ከመቀበል በስተቀር አማራጭ አል ነበረኝም።

የፈለገውን ከፈፀመ በኋላም ከዚያች ክፍል እንዳንንቀሳቀስ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በሩን ከውጪ በላያችን ላይ ዘግቶብን ሄደ። እኛም ፍርሃቱ ሙሉ በሙሉ እስኪለቀን ድረስ ከዚያች ክፍል ንቅንቅ አላልንም። ምንም እንኳን ሀብትና ንብረታችን ቢዘረፍ፣ በእኔ ላይ ያን መሰሉ በደል ቢፈጸም በሕይወት በደህና በመትረፋችን ሁላችንም አምላካችንን አመስግነናል።

በማግሥቱ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ ስለደረሰብን ግፍ አመለከትን። መቼም ያ ሰው እንደለመደው በእየተመላለሰ የፍትወቱ ማርኪያ እንደሚያደርገኝ የታወቀ ነው። ስለዚህ ከዚያ አካባቢ የምርቅበትን ሁኔታም ማመቻቸት አለብኝ። እስ ከዚያው ድረስ ግን ሌትም ሆነ ቀን እንቅልፍ በዓይኔ አልዞር ብሎ ተጨነቅሁ።

ደግነቱ ፓሊስ ያንን ወንጀለኛ ጠቁም ለሚያሳይ ሰው የአምስት ሺህ ዶላር ሽልማት እንደሚሰጥ ማስታወቂያ በማውጣቱ ሰውዬው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከአካባቢው እንደሚሠወር በመገመት በመጠኑም ቢሆን የሕሊና ዕረፍት አገኘሁኝ። መደበኛ ሥራዬንም መከታተሌን ቀጠልሁ።

አንድ ምሽት ስራዬ ላይ ውዬ ወደ አፓርትማዬ በመመለስ ላይ እንዳለሁ ያንን ወንጀለኛ እኔ ከተሳፈርኩበት አቶብስ ውስጥ አየሁት። እሱም የተቀመጠው ከሹፌሩ ጀርባ በመሆኑ፣ ከሾፌሩ ፊት ለፊት ባለውና ተሳፋሪውን በሚያሳየው መስታወት ውስጥ አይቶኝ ኖሮ ፈገግ ሊልልኝ ሞከረ። በሁኔታው ድንጋጤም መገረምም ሞላኝ ግን ለምን? ያለፈውን የፈጸመብኝን በደል በመርሣት ይቅርታ እንዳደርግለት አስቦ ይሆን? ይህ አረመኔ በእኔ ላይ ስለፈጸመው ግፍ ይቅር ለማለት ብችል እንኳ ከዚያ በላይ የሆነ መኅበራዊ ግዴታ ነበረብኝ። በለመደው ሁኔታ እየተዟዟረ በሌሎችም እንስት እህቶቼ ላይ ተመሳሳይ የጭካኔ ተግባር እንደሚፈፅም አያጠራጥርም። ቀስ ብዬ ከዚያ አቶብስ ላይ ተደብቄ በመውረድ በአካባቢው ላገኘሁት ፓሊስ ማሳወቅ ነበረብኝ።

እንደ ዕድልም በአጠገቤ በመኪና የሚዟዟሩ የፓሊስ ኃይሎች አግኝቼ ነገሩን እንደነገርኳቸው ወዲያውኑ አቶብሱን



በመከታተል ከሚቀጥለው ጣቢያ ላይ ያ የከፋ ሰው ሊያዝ ቻለ። እውነት ለመናገር እኔ በዚህ ሳቢያ የአምስት ሺውን ዶላር ሽልማት አገኛለሁ የሚል ሐሳብም ምኞትም አልነበረኝም። ሆኖም ግን ፈቃዱ የእግዚአብሔር ሆኖ በዚያን ንብረቴ ተዘርፎ ባዶ እጄን በቀረሁበት ወቅት ሰውየውን ያስያዝኩት እኔ በመሆኔ የብዙ ሺህ ብር ባለቤት ለመሆን በቃሁኝ።

እንግዲህ ተስፋዬ በጨለመበት ወቅት እግዚአብሔር ባልታሰበ መንገድ እጥፍ ድርብ አድርጐ ካሣኝ። የእግዚአብሔርን ፍቅርና አባትነት ይበልጥ ተረዳሁት፣ አመንኩበት። በጦርነት ከምትታመስ አፍሪካዊቷ ኢትዮጵያ አውጥቶ ከረሃብና ከጉስቁልና አላቆ እነሆ ለአሜሪካ ምድር ማብቃት ብቻ ሳይሆን ባልታሰበ መንገድ የሺህ ዶላሮች ባለቤት አደረገኝ።

# ምዕራፍ 16

## ዘለቄታዊ ትምህርት

እነሆ ረጂሙንና መራራውን ጉዞ ተጉዤለሁ። በመጨረሻም አምላኬና ጌታዬ ከድካሜ እፎይ ወደምልበት ሕይወት አድርሶኛል በብዙ መከራ ውስጥ ያለፍኩትን ያህል አሁን ባለሁበት ሁኔታም አንዳንድ ነገሮችን ለማለት እችላለሁ።

ከአሜሪካ ቆይታዬ አንድ ቀላል ሆኖም እጅግ ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ገብይቻልሁ። ይኸውም አንድ ሰው ቆርጦ ለመሥራት እስከፈለገ ድረስ ጨርሶውንም ሥራ በማጣት ችግረኛ እንደማይሆን ነው።

ለምሳሌ እኔ ያሻኝን ሥራ አማርጬ ለመያዝ እንቅፋት የሆነብኝ እንደልብ መጻፍና ማንበብ አለመቻሌ ይሁን እንጂ ከዚህ በተረፈ ግን ባለኝ ሙያ የመቀጠር ዕድል ያጣሁበት አንድም አጋጣሚ የለም። እርግጥ ውስጥ ውስጡን የሚያብሰለስለኝ ከትውልድ አገሬ ከመውጣቴ በፊት የትምህርት ቤት በር ረግጬ አለማወቁ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዕውቀት በትምህርት ቤት ግቢ ብቻ አለመወሰኑን በመገንዘብ በአያሌው ለመፅናናት ችያለሁ። ይህም በመሆኑ ነው በግሌ በመፍጨርጨር የራሴን ሕይወት የምታሳይ ብዩ የምገምታትንና



በእኔ የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ሌሎች ሊማሩ የሚችሉት ቢያንስ አንድ ነገር ይኖር ይሆናል ብዩ በማሰብ ይህቺን አነስተኛ መጽሐፍ ለአንባቢያን ለማበርከት የቻልኩት። በውስጤ ያለውን ሐሳብ የመግለጽ ዕድል በማግኘቴም ታላቅ ዕድለኛ ነኝ እላለሁ።

በዚህ አጋጣሚ የማስተላልፈው መልእክት ለአንዱ አንባቢ ጥሞ ሌላውን ባይማርከውም ዞሮ ዞሮ ውስጣዊ ስሜቴን በዚህ መልኩ ለማስፈር በመቻሌ ለአምላኬ ታላቅ ምስጋና አቀርባለሁ። እናንተም አንባቢዎቼ እግዚአብሔር ለእኔ የለገሠውን ይህን ዕድል ለእናንተም እንዳይነፍጋችሁ የዘወትር ጸሎቴ ነው።

እግዚአብሔር የእኔን ሕይወት በብዙ ውጣ ውረድና ፈተና ውስጥ አሳልፎ ለዚህ ማብቃቱ የሚከተለውን መልእክት ለሕዝብ እንዳስተላልፍ በጐፈቃዱ በመሆኑ ነው።

«እግዚአብሔር አሜሪካንን የባረከና የቀደሳት፡ በመሠረቱ አሜሪካውያንን ከሌሎች ሕዝቦች አብልጦ በመውደዱ ወይም አሜሪካውያን ከሌላው የዓለም ሕዝብ የተሻሉ በመሆናቸው አይደለም። ዳሩ ግን አሜሪካ ለእንደእኔ ላሉ የተገፉና የተጐሳቆሉ ስደተኞች መሰባሰቢያና አለኝታ እንድትሆን ቀድሞውኑ በመፈለጉና በማቀዱ ነው። ነጮና፡ ጥቁር፡ ቢጫና

ቀይ ሕዝቦች ጐን ለጐን በመሰለፍ በሰላም ሠርተው እንዲተዳደሩባት የመረጣት አገር በመሆና ነው።

«እግዚአብሔር መንግሥታትን ቢቀያይርና እስከጭራሹም ቢደመስሳቸውም ሕዝቦቹን ግን ለጥፋት አይዳርግም። በንጉሥ ሰሎሞንና በንግሥት ሳባ ዘመን መንግሥት ኢትዮጵያ ሰፊ ግዛትን የምታካልል ሀያል አገር ነበረች። ዛሬ ደግሞ ለረሃብና ለድርቅ ለመከራና ለሥቃይ ተዳርጋ የሌሎች መዘበቻና መተረቻ ሆናለች። ያም ሆኖ ግን እግዚአብሔር ሕዝቧን ሙሉ በሙሉ ረስቶታል ማለት አይደለም። አሁንም በኢትዮጵያ ውስጥ እራሳቸውን ለአምላካቸው በማስገዛት መንፈሳዊ ሕይወት የሚመሩ አያሌ ብፁአን ሰዎች ይገኛሉና።

እነኝህ ሰዎች ተለዋዋጭ በሆነው ሰው ሠራሽ መንግሥት ቅርፅና ገፅታ ሳይደለሉ እራሳቸውን የሚያስገዙት ለአንዱና ለብቸኛው እግዚአብሔር ነው። እነርሱም እግዚአብሔርን እንዳልረሱት ያህል፣ እርሱም ሙሉ በሙሉ ለጥፋትና ለውድመት አያጋልጣቸውም። አሜሪካ፣ ሌሎችን ችግረኞች ለመርዳት ፈቃደኛ ሆና እጇን በመዘርጋቷ እግዚአብሔርም በእቅፉ ሥር አድርጐ ይንከባከባታል። ሆኖም ግን የተሰደድትን የተራቡትንና የታረዙትን ለመርዳት ፈቃደኛ ሳትሆን በሯን ብትዘጋ በዚያው ልክ የአምላክ በረከትና ፀጋም ይሸሻታል።



እግዚአብሔር በአሜሪካ አማካይነት የተናቁትንና የተጠሉትን፣ የተገፉትና የተበደሉትን ሕዝቦች በማሰባሰብ እንባቸውን ከዓይናቸው ያደርቃል። የጠወለገ ሕይወታቸውንም ያለመልማል።»

# ድህረ ታሪክ

እነሆ እኔ በአሁኑ ወቅት በአሜሪካ ውስጥ የተረጋጋ ሕይወት በመምራት ላይ እገኛለሁ። መንፈሳዊ ሕይወቴን በተመለከተ በኖርፎልክ፣ ቨርጂኒያ ውስጥ በሚገኘው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን ከአንድ ምዕመን የሚጠበቀውን አገልግሎት በማበርከት ላይ ስገኝ፣ በተጨማሪም የቨርጂኒያ ግዛት መከላከያ ኀይል ባልደረባ በመሆን የሦስት ዓመት ግዳጄን ተወጥቻለሁ። በሌላም በኩል፣ በወጥመድ የተያዘች ወፍ *(Bird in a Cage)* እና የጥላ ውዝዋዜ *(Shadow Dance)* በሚባሉት ሁለት ፊልሞች ውስጥ ተዋናይ የመሆን ዕድልም አግኝቼአለሁ።

ከእንግዲህ የቀረኝ የማገኘውም አሜሪካዊ ህልም የሆነውን የግል መኖሪያ ቤቴን ከአንድ ባህር ዳርቻ መሥራት ነው። ከዚያም በነጋ በጠባ በዳክዬና በባህር አእዋፍ ጫጫታ ከእንቅልፌ መቀስቀሱን፣ የባህሩን ሞገድ ድምጽ በመስማት በአረምሞ መመሰጡን በታላቅ ናፍቆት የምጠባበቀው ነው።

ቤቴም የእግዚአብሔርን ስምና ክብር በሚያወድሱ መዝሙሮችና ሙዚቃዎች ቃናና እንጉርጉሮ የተሞላ ይሆናል። ምናልባት ዕድሌ ተሳክቶ፣ ቤቴን እንዲያዩልኝ ከምጋብዛቸው



እንግዶች አንዱ እርስዎ ቢሆኑ፣ ከበራፌ እንደደረሱ በሀገሬ ባህል መሠረት በመጀመሪያ እቅፍ አድርጌ ጉንጮችዎን እስማለሁ። ከዚያም ስለ ቤተሰብዎ ደህንነት እንዲያወጉኝ አንዳንድ ጥያቄዎች አቀርብልዎታለሁ። የሚቀጥለው ሥነ ሥርዓት በአገራችን ትልቅ ክብር የሚሰጠውና ለሚወዱት እንግዳ የሚዘጋጀውን ግብዣ ቡና ማፍላት ይሆናል።

የአፈላሉ ሥነ ሥርዓት የራሱ የሆነ ውበት ስላለው እንደሚደሰቱበት አልጠራጠርም። ልዩ ልዩ አድሩሶችንና ሰንደሎችን በማጫጫስ ለቤቱ ጠረን ጣፋጭ የሽታ መዓዛ ማላበስ ነው።

ለቡናው ማጣጫ የሚሆን ቁርስ ማቅረብ ደግሞ ሌላው ግዴታዬ ነው። ምናልባትም እንደ ፈንደሻ ዓይነት የቡና ቁርስ አለበለዚያም እንጀራ በበርበሬ አለዚያም በአዋዜ እየተመተሙ እንዲበሉ ባቀርብልዎት ደስ ይለኛል። አንዳንዶች እንደሚሉት ጣሊያኖች ፒሳን መስራት የተማሩት እኮ! የእኛኑ እንጀራ አለዚያም አነባበሮን አይተው ሳይሆን እንዳለቀረ ነው።

በሃገራችን ለትዳር ከፍተኛ ከበሬታ የሚሰጠው ስለሆነ ቡና በሚጠጣበት ወቅት አዘውትሮ ስለትዳር ጓደኛ ደህንነትና ስለ ልጆችም ሁኔታ ይነሳል። እኔም ቡናዬን እየጠጡ ስለዚሁ



ጉዳይ እንዲያጫውቱኝ እጋብዞዎታለሁ። የሃገሬን ባሕል በማስመልከት አንዳንድ ነገሮችን መጻፌ አንባቢዎቼን ለማሰልቸት ሳይሆን ስለማያውቁት ኢትዮጵያ ባህልና ወግ ለውጪዎቹ በመጠኑም ቢሆን እውቀት ለመፈንጠቅ ነው።

ምንም እንኳን ቀደም ሲል እንደገለጽኩት በአሜሪካ ሕይወቴ እጅግ ደስተኛ ብሆንም ስለ ኋላ ቀሯ አፍሪካ በአስብኩ ቁጥር ግን ማዘንና መጸጸቴ አይቀርም። እርግጥ በአሜ



ሪካንም ውስጥ ቢሆን አልፎ አልፎ ጭቆናና በደል ይፈጸማል። ሆኖም እንደአፍሪካ የእርስ በርስ ውጊያ፣ ግድያ፣ ዝርፊያና ጥላቻ የሚንፀባረቅበት ሌላ አህጉር የለም። ኢትዮጵያ የገናናውና ታላቁ የንጉስ የሰለሞንና የዝነኛዋ ንግስት የንግስት ሳባ ግንኙነት ውጤት የሆነች ረጅምና አኩሪ ታሪክ ያላት ሃገር ናት። ያም ትውልድ ሲወራረድ ቆይቶ እነሆ ከአሁኑ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያኖች ላይ ደርሷል። እንግዲህ ይህን ታሪክ ሳንረሳው ሁላችንም ተባብረን ለታሪክ መዘክርም ብሩህ የሆነ ውርስ አስረክበን እንለፍ። መላው የዓለም ሕዝብም ለዚህ ታላቅ አላማ እንደሚተባበረን የምንጊዜም ፀሎቴ ነው። በመጨረሻም ሁላችሁንም ከልብ እንደማፈቅራችሁ ለመግለጽ እወዳለሁ።

እወዳችኋለሁ

መዲና

# የተናቁ ዕንቊዎች…

## እንደ ፈርጥ በሚንተገተጉት ምጥን ገጾቿ ፡—



መዲና ገ/ማርያም

* የሽብርና ንውጽውጽታ፡— የረ ሀብና ጦርነት አውድማ ከሆነችው ኢትዮጵያ "ሰላምና ብልፅግና ወደ ሰፈነባት" ምዕራባዊቱ አገር በማ ሸጋገር ፡ የእግዚአብሔርን መንከ ራትና ታምራት፡— የእርቅና ፍቅርን ምሥራች ታበስራለች ።

## አሁንም ብነዚያው ገጾቿ፡—

* የዘር ሐረጓ በቀጥታ ከንግሥት ሳባ የሚጠቀሰው መዲና እንደምን በስድስት ዓመቱ የጨቅላ ዕድሜዋ ለባርነት እንደተሸጠች …
* ሌሊቱን፡— እንደከብት በበረት ታጉራ ከምታድርበት ቀኑን
  – እንደባተለችና እንደቃበዘች ከምትውልበት ጣርና ጭንቅ አምልጣ ከአገር አገር እንደ ተሰደደች…
* እንዲያም ብሎ በአውሮፓና አረቢያ ቤተ መንግስታት የልዕልታትና ልዑላን አቻነቷን ታሳዩናለች።

## በመጨረሻም ፡

ለተናቀውና ለተረሳው ዳሩ ግን ወደር ለማይገኝለት አኩሪው ኢትዮጵያዊ ወግና ባህል ማንሰራራት መዲና በአሜሪካ ሽንጧን ገትራ ስለመሟገቷ ታስነብበናለች።